# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት






**የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለትራንስፎሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት**

መጋቢት 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ማውጫ ..................... i

ክፍል አንድ ..................... I

መግቢያ ..................... 1

የኤጀንሲው ዓላማ ..................... 3

የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር ..................... 3

የምክር ቤቱ (ቦርዱ) ሥልጣንና ተግባር ..................... 4

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ..................... 5

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ ..................... 5

ኦዲቱ ዓላማ ..................... 6

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ..................... 6

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ..................... 6

ክፍል ሁለት ..................... 9

የኦዲት ግኝቶች ..................... 9

2.1 ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥናትና በምርምር በመለየት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡ ..................... 9

ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በጥናት የለየና ችግሮቹ የሚፈቱበትን ስልት ነድፎ መተግበሩን በተመለከተ፣ ..................... 9

ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ጥናቶች ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እና ተግባራዊ መሆናቸውን በተመለከተ፡- ..................... 17

ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው ቦታዎች ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ማዘጋጀቱን በተመለከተ፡- ..................... 19

ኤጀንሲው የሚመራቸው ፕሮጀክቶች ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች ማለፋቸውን በተመለከተ፣ ..................... 21

ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚጠናቀቁ ስለመሆኑ፣ ..................... 22

ኤጀንሲው ወደ ተግባር ባለቤቶች የሚተላለፉ ፕሮጀክቶችን ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ ..................... 32

ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ሶስት የግምገማ ምእራፎችን ማለፋቸውን በተመለከተ፣ ..... 33

ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት አፈጻጸማቸው ላይ ግምገማ ማድረጉን በተመለከተ፣ ..... 34

2.2 ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት፣ ከአገር አቀፍና ከአለም አቀፍ የግብርና ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፣ ..... 36

የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ ..... 36

ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ የሚያስችል ዕቅድ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ..... 38

ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ለማስፈጸም የሚያከናውናቸው ተግባራትን መገምገሙን በሚችልበት መንገድ ማስቀመጡን በተመለከተ፣ ..... 38

ኤጀንሲው የተግባር ባለቤቶች የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ያጠና መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 39

ለትራንስፎርሜሽን አጀንዳ የተግባር ባለቤቶች የተደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ፣ ..... 40

በሙከራ (Pilot) ደረጃ ተሞክረው የስራው ባለቤት እንዲያስፋፋቸው የተደረጉ ስራዎች መኖራቸውን በተመለከተ፣ ..... 42

በትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት ዙሪያ ፈፃሚ አካላት ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉን በተመለከተ፣ ..... 43

ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 44

በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እና የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር መፈጠሩን በተመለከተ፣ ..... 45

ክፍል ሦስት ..... 48

መደምደሚያ ..... 48

ክፍል አራት ..... 51

የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 51

አባሪ 1፡ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር ..... 54

አባሪ 2፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ ..... 55

አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላትና ፕሮጀክቶች ዝርዝር ..... 58

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery)

የኢትዮጵያ መንግስት በግብርናው ዘርፍ ያሉ ማነቆዎችን ለሚፈቱ ወሳኝ ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት የግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳን ይፋ በማድረግ ራሱን የቻለና በግብርናው ዘርፍ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ የተፋጠነ እንዲሆን ሊያደርግ የሚችል የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ እንዲቋቋም አድርጓል።

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለትራንስፎሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል አፈፃፀምን በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተመልክተዋል፡፡ እነርሱም፡-

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ መስጠትና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ አለመቻሉ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚያደርጋቸው ጥናቶች የአነስተኛ አርሶ አደሩን እና የፈፃሚዎችን ፍላጎት እና አቅም መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን የትግበራ ቅድመ-ዝግጅት (Implementation set-up) ሙከራና ማሻሻያ (testing and refinement) እና ማስረከብ (handover) የሚሉ ሶስት የትግበራ ደረጃዎች እንዲያልፉ ስለማድረጉ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው በናሙና ተመርጠው ከታዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የረጅም ጊዜ ተግባር ባለቤት (deliverable owner) ያስተላለፈው ፕሮጀክት የሌለ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ወደ ሚመለከተው የተግባር ባለቤት የሚተላለፉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚከታተልበትና ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በየአመቱ እና በአመት ሁለት ጊዜ ውጤታማነታቸውን እና

ያስገኙትን ስኬት ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት የማይገመግም መሆኑ፣

- ኤጀንሲው በስትራቴጂዎች ውስጥ የተቀመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች (የፖሊሲ ማሻሻያ፣ አሰራሮች) ባለድርሻ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በሚተገብሩበት ወቅት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣
- የሰብል ምርትና ምርታማነት ይረዳሉ ብሎ ያዘጋጃቸው (የገብስ፣የጤፍ፣ስንዴ፣በቆሎ ወ.ዘ.ተ) ስትራቴጂዎች በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች አለመላኩን እና እነዚህን ስትራቴጂዎች በአገራችን ቋንቋዎች (በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ ወ.ዘ.ተ) ተተርጎሞ ለተጠቃሚው ምቹ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጁ ያላደረገ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ የሚያከናውናቸው ተግባራት በመለየት ለመፈፀም የሚያስችል ዝርዝር ተግባራትን የያዘ የራሱ እቅድ የሌለው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የተግባር ባለቤቶች የሚያስፈልጋቸውን የድጋፍ ዓይነት ለማወቅ የሚያስችለው የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ያላጠና መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ከክላስተሪንግ በስተቀር በፓይለት ደረጃ ተሞክሮ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ያደረገው ስራ አለመኖሩ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ ላላቸው አካላት የሚያዘጋጃቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የወጣ ወጪ እና የተሳታፊዎችን ስታስቲካዊ መረጃ እንዲሁም ከተፈጠሩ መድረኮች በተግባራት አፈፃፀም ላይ የተገኘውን ውጤት የሚገመግምበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በትራንስፎሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ አስመልክቶ ሪፖርታቸውን በማጠናቀር ለትራንስፎርሜሽን ካውንሱሉ ከመላክ ውጪ ፈፃሚዎች በየጊዜው ያሉበትን ደረጃ በጋራ እየገመገመ አፈፃፀማቸው ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚቻል እና ኤጀንሲው ግብርናውን ማዘመን የሚያስችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ የሚችል መሆኑን በኦዲቱ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- ኤጀንሲው ለሰብል ምርትና ምርታማነት እድገት ማነቆ የሚሆኑ ችግሮች በተደጋጋሚ ሊከሰቱ የሚችሉ በመሆናቸው ችግሮችን በየጊዜው በጥናት ሊለይ ይገባል፡፡ ችግሮችን ለመፍታት የሚነድፋቸው ስልቶች አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ሊያደርግና አገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ያላትን አስተዋፅኦ እንዲጨምር ሊያደርግ በሚችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን በሶስቱ የትግበራ ደረጃዎች ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት በማጠናቀቅ እና የረጅም ጊዜ ባለቤቶች በራሳቸው ሊፈፅሙ እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ድጋፍ በማድረግ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሚደረጉባቸው ወረዳዎች የሚገኙ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለማሳካት የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጠቃሚ እንደሆኑ አምኖ የመረጣቸውን ፕሮጀክቶች ሙከራ በተቀመጠላቸው የጊዜ በማጠናቀቅ የረጅም ጊዜ ባለቤቶች እንዲያስፋፉ ሊያስተላልፍና የተግባር ባለቤቶቹ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት በአመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ በመገምገም ፕሮጀክቶች ያሉባቸውን ግድፈቶች በወቅቱ እንዲያስተካክሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት ለመደገፍ የሚያስችለውን ዝርዝር ተግባራትን የያዘ እቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ወደ ተግባር በመግባት አፈጻጸሙን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ሊያስቀምጥ ወይም

የአጀንዳው ባለቤቶች እንዲያስቀምጡ ድጋፍ በማድረግ እቅድና አፈፃፀሞችን በማነፃፀር የተገኙ ድክመቶች በወቅቱ እርምት እንዲሰጥባቸው ማድረግ አለበት፡፡

- ኤጀንሲው ለትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ ፍላጎታቸውን በየጊዜው በማጥናት ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ ላላቸው አካላት የሚያዘጋጃቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የወጣ ወጪ እና የተሳታፊዎችን ስታስቲካዊ መረጃ እንዲሁም ከተፈጠሩ መድረኮች በተግባራት አፈፃፀም ላይ የተገኘውን ውጤት የሚገመግምበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ውጤታማ ለማድረግ ከሚሰሩም ሆነ ግብርናውን ለማዘመን በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ በግብርና ላይ የሁሉም አካላት ተሳትፎን በማጠናከር በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው አገሪቱ ልትደርስ ያቀደችው ግብ እንዲመታ የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ባለፉት 10 ዓመታት በዓለም ላይ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ካሳዩ አገራት ተርታ የሚያስቀምጣትን ዕድገት ያስመዘገበች ሲሆን ከ1987-1997 ዓ.ም የነበረው ዕድገት 63 በመቶ ሆኖ ከ7.6 ቢሊዮን ወደ 12.4 ቢሊዮን ዶላር ያደገ ሲሆን ከ1997 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም የአገሪቱ ጠቅላላ አገር ውስጥ ምርት ከአራት ዕጥፍ በላይ ጨምሮ ከ12.4 ወደ 55.6 ቢሊዮን ዶላር ማደጉን ማስረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለዚህ ዕድገት መገኘት ዋና ዋና ምክንያቶች በትምህርት፣በጤና፣ በውሃ፣ በመንገድ ትራንስፖርት እና መገናኛ ዘርፎች የተደረጉ መዋቅራዊ እና የፖሊሲ ለውጦች ሥር ነቀል ቢሆኑም በዋናነት ግን የአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው የግብርናው ዘርፍ ዙሪያ የተካሄዱት ለውጦች ናቸው።

2. የግብርናው ዘርፍ ከአገሪቱ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) በግምት 40 በመቶውን እና ከአገሪቱ የሥራ እድል ውስጥ ወደ 70 በመቶ የሚሆነውን የሚይዝ እንደመሆኑ እንደ ሁልጊዜው በመንግስት የኢኮኖሚ ልማት ስልት ውስጥ ወሳኝ ክፍል እንደሆነ ይገኛል። ምንም እንኳን ካለፉት ዓሥርት ዓመታት በላይ የግብርናው ዘርፍ ቋሚ ዓመታዊ ዕድገት ቢያሳይም ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ግብርና እና የአርብቶ አደር ልምዶች እንደተዋጠ ይገኛል። በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ሂደት ውስጥ የሚታየው አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮቻችን ከዚህ ከእጅ ወደ አፍ ግብርና ወደ ገበያ ተኮር እና ሰፋ ወዳለ የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን የሚያደርጉት ሽግግር ነው። የግብርናው ዘርፍ ይህንን ሽግግር እንዲያካሂድ ለፈጣን መፍትሔዎች እጅ የማይሰጡ ስር የሰደዱ የአወቃቀር ተግዳሮቶችን መዳሰስ አለበት። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ መንግስት መሰል ማነቆዎችን ለሚፈቱ ወሳኝ ሥራዎች ቅድሚያ ለመስጠት የግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳን ይፋ አድርጓል።

3. በጥር ወር 2001 ዓ/ም በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር እና በቢል ኤንድ ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን (Bill and Melinda Gates Foundation) መካከል የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ እንዲሻሻል ለማድረግ የሚያስችል የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓት ላይ የስትራቴጂ ክለሳ በፋውንዴሽኑ እንዲደረግ ስምምነት ተደርሶ ክለሳው ተከናውኑ የውጤቱ ሪፖርት በመስከረም 2001 ቀርቧል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት

የግብርናው ዘርፎች ላይ በተጠናቀቀው ሪፖርት መሰረት በፋውንዴሽኑ ድጋፍ እንዲደረግለት ፍላጎቱ መሆኑን በማሳየቱ ፋውንዴሽኑ በኢትዮጵያ የግብርና ስርዓቱ ላይ ዝርዝር ጥናት አከናውኖ በነሀሴ 2002 ዓ/ም ሰባት የሚሆኑ ሪፖርቶችን ለመንግስት አቅርቧል፡፡ በሪፖርቱ ከተሰጡት ሀሳቦች መካከል አንዱ ራሱን የቻለና በግብርናው ዘርፍ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ የተፋጠነ እንዲሆን የሚያደርግ አካል ማቋቋም የተሻለ እንደሚሆንና ይህ አሰራር እንደ ታይዋንና ደቡብ ኮሪያ በመሳሰሉት ሀገሮች ላይ ውጤታማ እንደሆነ የሚገልፅ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም የፋውንዴሽኑ ሀሳብ ተቀብሎ በታህሳስ ወር 2003 ዓ/ም የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 198/2002 ተቋቋመ፡፡ ይህ አዋጅ በደንብ ቁጥር 380/2003 ተሻሽሏል፡፡

4. የኤጀንሲው የበላይ አመራር የግብርና ትራንስፎርሜሽን ካውንስል ሲሆን ይህ ካውንስል የሚመራው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ተጠሪነቱ ለእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ነው፡፡

5. በዚህም መሰረት ኤጀንሲው ስድስት ፕሮግራሞችን (production & productivity, Agribusiness & markets, sustainable & inclusive growth, enhanced implementation growth, agricultural commercialization clusters, analytics) በመያዝ እና በአራት ደረጃዎች (Phases):-

- **ምዕራፍ አንድ** Inception **የመጀመሪያው ዕ.ት.ዕ ምስረታ** 2003-2007

  በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የዋና ሰብሎችን ምርት በ2005 ዓ.ም ከነበረበት በእጥፍ ማሳደግና እሴት መጨመርን 8 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት አስተዋጽኦ ማድረግ ነበር፡፡

- **ምዕራፍ ሁለት** Impact **ሁለተኛ ዕ.ት.ዕ ውጤት** 2008-2012

  ሁለተኛው ምዕራፍ በምስረታ ምዕራፍ ውስጥ የተገኙትን ተሞክሮዎች ከፍተኛ ውጤት ወደሚያስገኙና በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ በሰፊው ወደሚተገበሩ የመፍትሄ ሃሳቦች ማስፋት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ምዕራፍ የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ ከምርት ተኮር አሰራር በከፍተኛ ሁኔታ የገበያ ጉዳዮችን ወደ ሚያካትት አሰራር ማሸጋገር ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋል፡፡

- **ምዕራፍ ሦስት** Impact **ዕ.ት.ዕ ውጤት** 2013-2017

በመጀመሪያውና ሁለተኛው ምዕራፎች በሚገኙት ስኬቶችና በሚቀሰሙት ተሞክሮዎች ላይ በመመስረት የሶስተኛው ዕ.ት.ዕ የውጤት ምዕራፍ (ከ2013-2017) የኤጀንሲው ድጋፍ መጠነ ሰፊ ወደሆኑ የምርትና የገበያ ተኮር የአጀንዳ ተግባራት እንደሚያስፋፋው ይጠበቃል፡፡

- **ምዕራፍ አራት** Transition **ዕ.ት.ዕ ውጤት 2013-2017**

በዚህ ጊዜ በኤጀንሲው ሲከናወኑ የቆዩ አብዛኞቹን ተግባራት የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የአሁን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በባለቤትነት እንደሚረከብና፣የኤጀንሲው ሚናም ድጋፍ የመስጠት እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ይህ የመጨረሻ ምዕራፍ የቁልፍ ምርቶችን ምርታማነት የእስያና የደቡብ አሜሪካ ሀገራት የምርትና ምርታማነት ደረጃ ላይ የማድረስ፣እንዲሁም በምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ የሚኖረውን ህዝብ ወደ 10 በመቶ ወይም ከዚያ በታች ለማድረስ አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ

6. ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-
   - የግብርና ልማትን ቀጣይነት ለማረጋገጥና መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ማፈላለግና ተግባራዊነቱን መደገፍ፣
   - የግብርና ልማት አፈጻጸም ውጤታማነት እንዲረጋገጥ በግብርና እና ተዛማጅ ተቋማት መካከል እንዲሁም የግብርና ልማትን ለመደገፍ በሚቀረጹና በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲኖር ማድረግ፣

   ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

7. ኤጀንሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 198/2002 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 380/2008 መሰረት ፡-

   ሀ/ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፣

   ለ/ የሰብልና እንስሳት ሀብት ግብርና ምርትና ምርታማነት መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩና የሚፈቱበት ስልት እንዲነደፍ ያደርጋል፣አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

ሐ/ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን ግብይት ለማሳደግና እሴት ለመጨመር የግብርና ንግድና ግብይትን መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩ ያደርጋል፣ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

መ/ ዘላቂና አሳታፊ የሆነ የአካባቢ ጥበቃና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፣አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ሠ/ ግብርናን አስመልክቶ የሚከናወኑ ሥራዎችን በአግባቡ ለመፈጸምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ተቋማዊ አቅምን ለማሳደግ መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት እንዲለዩ ያደርጋል፣የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ረ/ የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማቀላጠፍ በትኩረት የሚፈፀሙና ቅድሚያ የተሰጣቸው ተግባራትን ዝርዝር ያዘጋጃል፤

ሰ/ በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ መሠረት ከምክር ቤቱ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ፕሮጀክቶችን ያስተዳድራል፤ይመራል፤

ሸ/ የግብርና ልማት አፈጻጸምን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረጹ ፕሮጀክቶች መካከል መልክዓ ምድር መሠረት ያደረገ ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

ቀ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በራሱ ስም ይከሳል፣ይከሰሳል፤

በ/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

የሚሉ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቷታል፡፡

**የምክር ቤቱ (ቦርዱ) ሥልጣንና ተግባር**

8. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 198/2002 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 380/2008 መሰረት ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የግብርና ልማትን ውጤታማነት የሚገቱ መሰረታዊ ማነቆዎች እንዲለዩ፣ የሚፈቱበት ስልት በአግባቡ እንዲቀመጥና በውጤታማነት እንዲተገበር የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣

ለ) በግብርና ልማት ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ከፍተኛ ቅንጅታዊ

አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫና አመራር ይሰጣል፣

ሐ) የኤጀንሲውን እቅድ ያጸድቃል፣አፈፃፀሙን ይገመግማል፣ እንደአስፈላጊነቱ የስራ መመሪያ ይሰጣል፡፡ ምክር ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል**

**ድርጅታዊ መዋቅር**

9. ኤጀንሲው በአንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚመራ ሲሆን በስሩ አንድ አንድ ሲኒየር የመንግስት እና የህዝብ ጉዳዮች ሃላፊ፣ የስነ ምግባር ኦፊሰር እና የውስጥ ኦዲት ሃላፊ እንዲሁም በሰባት ሲኒየር ዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ሲሆን በሰባቱ ሲኒየር ዳይሬክቶሬቶች ስር በአጠቃላይ 29 ዳይሬክቶሬቶችን በማካተት የተዋቀረ ነው፡፡ **የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡**

**የኤጀንሲው የሰው ሃይል**

10. ኤጀንሲው እስከ ታህሳስ 2010 ዓ.ም ድረስ 98 (26%) ሴት ሰራተኞች 266 (74%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 364 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን፣ ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ፒኤችዲ 11 (4%)፣ ማስተርስ 131 (35%)፣ ዲግሪ 136 (37%)፣ ዲፕሎማ 29(8%) እና ከዛ በታች ያሉ 57(16%) ናቸው፡፡

**የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ**

11. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 198/2002 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 380/2008 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈፀም ይረዳው ዘንድ ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከለጋሽ ድርጅቶች እርዳታ እና ከአለም ባንክ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት በኩል ብድር የሚያገኝ ሲሆን ከ2007-2010 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀት፣ የተሠጠው እርዳታ እና ያገኘው ብድር ውጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | ከመደበኛ በጀት | | | ከለጋሽ ድርጅቶች | | | ብድር (AGP ከአለም ባንክ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት በኩል የተገኘ) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደ | ስራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በ% | የተሰበሰበ | ስራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በ% | የተገኘ ብድር | ጥቅም ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በ% |
| 2007 | 39,833,719 | 39,833,719. | 100 | | 218,109,914 | 57.0 | 132,281,13 | 117,334,77 | 88.70 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | .00 | 00 | % | 382,250,966.00 | .00 | 5% | 6 | 1 | % |
| 2008 | 45,626,491.00 | 45,471,501.00 | 99.6% | 422,584,083.00 | 331,606,289.00 | 78.47% | 190,927,885 | 142,068,174 | 74.40% |
| 2009 | 93,830,233.00 | 72,719,731.46 | 31.41% | 342,603,689.00 | 469,164,169.43 | 136.94% | 86,449,337.09 | 97,411,625 | 112.68% |
| 2010 | 175,757,956.20 | 30,588,950.05 | 17.40% | 285,839,951.51 | 118,524,410.95 | 41.46% | 12,000,000 | 2,963,927.77 | 24.69% |

**የኦዲቱ ዓላማ**

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ መሰረታዊ የአሰራር ስርዓት ማነቆዎችን በጥናት መለየታቸውን እና ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የሆኑ ስልቶች ተነድፈው፣ ቁጥጥር ተደርጎባቸው እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማነቆዎቹ ውጤታማ በሆነ መልኩ የተፈቱ እና የተተገበሩ መሆኑን ማጣራት ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

**ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)**

13. "ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለትራንስፎሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

**የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች**

**የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች**

14. ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን በሁለቱም የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች (Sub-Issues) ተለይተዋል፣ እነርሱም፡-

   1. ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥናትና በምርምር ለመለየት እንዲሁም ፕሮጀክቶችን ለመቅረጽ እና

ተግባራዊነታቸውን ለመከታተል የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤

1.1 ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች መከናወናቸውን እና የሚፈቱበትን ስልት በመቀየስ እንዲተገበሩ ማድረጉን መገምገም፣

1.2 ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ፕሮጀክቶችን የሚቀርጽበት፣ የሚተገበርበትና ክትትል የሚያደርግበት እንዲሁም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

2. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ እና ፕሮጀክቶችን ለሚተገብሩ አስፈፃሚ አካላት (Deliverable owners) የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን ማጣራት፣

2.1 ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ የትራንስፎሜሽን አጀንዳዎችን ለሚተገብሩ አስፈፃሚ አካላት (Deliverable owners) ድጋፍ የሚያደርግ እና አፈፃፀማቸውን የሚከታተል መሆኑን መገምገም፣

2.2 ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት (የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ፣የክልል ግብርና ቢሮዎች፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የህብረት ስራ ኤጀንሲዎች ወዘተ) ፣ ከአገር አቀፍና ከአለም አቀፍ የግብርና ተቋማት ጋር የሰብል ምርትና ምርታማነትን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሠራበት አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች**

15. ከላይ የተለዩትን ሁለት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 20 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅቷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንቦች ቁጥር 198/2002 እና 380/2008፣

የግብርና ትራንስፎርሜሽን አፈፃፀም ሪፖርት ከ2003-2007፣ የግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ የ2008 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት፣ የንግድ መር እርሻ አገልግሎት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የ2008 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት፣ የኤጀንሲው የፕሮጀክት እቅድ፣ ትግበራ፣ ቁጥጥርና ግምገማ መመሪያ፣ የሁለተኛው ምዕራፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ የኢትዮጵያ ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የአሰራር መመሪያ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁትም መመዘኛ መስፈርቶች ለኤጀንሲው ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ **የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡**

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

16. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2007 እስከ 2010 የመጀመሪያው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያሉትን የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

17. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ሲሆን በተጨማሪም ከኤጀንሲው ጋር በቅርበት ከሚሰሩ በናሙና ከተመረጡት የኦሮሚያ፣ የደቡብና የትግራይ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች እና ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች እና ከላይ በተጠቀሱት ክልሎች ከሚገኙ ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ከሚያደርግባቸው ወረዳዎች በናሙና ከተመረጡ ሰባት የፕሮጀክት አይነቶች ማለትም (የምጥን ማዳበሪያ፣ የግብርና ግብአት መከታተያ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የቀጥታ ዘር ግብይት፣ የገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም፣ የግብርና አገልግሎት ማዕከል ግንባታ እና የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት) ውስጥ በደቡብ ክልል ሰባት፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ሶስት ሶስት በአጠቃላይ ለ13 ፕሮጀክቶች የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ማስረጃዎችን በመከለስ እና የመስክ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡ **በኦዲቱ ወቅት የታዩ ባለድርሻ አካላትና ፕሮጀክቶች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡**

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### 2.1 ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥናትና በምርምር በመለየት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

**ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በጥናት የለየና ችግሮቹ የሚፈቱበትን ስልት ነድፎ መተግበሩን በተመለከተ፣**

18. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በጥናት ሊለይ ይገባል፡፡ የተለዩት ችግሮች የሚፈቱበትን ስልት ሊነድፍ፣የሚነድፉቸው ስልቶች ዕድገትን፣አካባቢያዊ ዘላቂነት፣ አስተማማኝ የገበያና የምርት ማቀነባበር ብቃት እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ሊያካትቱና በጥናቱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና የትግራይ ክልሎች የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የተከናወኑ ጥናቶችን በተመለከተ፡-

    - ኤጀንሲው በ2008 በጀት ዓመት የግብርና የምርት ማቀነባበሪያን ማስተዋወቅና የምርት ማቀነባበርን አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እና የባለድርሻ አካላት ምክክር በማድረግ፣ የድርጊት መርሃ ግብር ማዕደቅን አቅዶ ያላከናወነ ሲሆን በ2009 እና 2010 በጀት ዓመትም በዕቅዱ እንዲካተት ያላደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፣

20. ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይ ያሉ ችግሮች በመለየት አስፈላጊውን ስልት በመንደፍ ችግሮቹን መፍታት የሚገባው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት፡-

    - የግብዓት አቅርቦት (ምርጥ ዘሮች፣ ማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣ የፀረ ተባይ እና አረም መደሃኒቶች) በወቅቱ እና በበቂ ሁኔታ ለአርሶ አደሩ የሚቀርብበትን ሁኔታ አለመመቻቸቱ፣
    - የአርሶ አደሩን የግብአት ፍላጎት ለማወቅ የደሰሳ ጥናት አለማድረግ እና የግብርና ግብአት ፍላጎት በግብርና ባለሞያዎች በአግባቡ ያለ መለየት አርሶ አደሩም ያለው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ በቂ የሆነ ግብአት እና ቴክኖሎጂ ያለመጠቀም ሁኔታ መኖሩ፣

- የገጠር ፋይናንስ የአቅርቦት ጥራትን በተመለከተ ብድር በወቅቱ አለማግኘት፣ የቁጠባ ወለድ መጠኑ አበረታች አለመሆን፣ ግብርናው ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ተጋላጭ በመሆኑ አበዳሪዎች ብድር ለመስጠት ፍላጎት አለመኖር፣ አገልግሎቱ በሞባይል ባንኪንግ አለመሆን፣ የብድር ሰጪ ተቋማት በገጠር ቀበሌዎች ተደራሽ አለመሆን እና ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ስለገጠር ፋይናንስ በቂ እውቀት የሌላቸው መሆኑ፣
- በአርሶ አደሩ አካባቢ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አለመኖር እና ገበያ ተኮር ምርት ማምረት አለመቻሉ፣
- አዳዲስ የሚከሰቱ አረሞችና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚመጡ ችግሮች በወቅቱ እየተፈቱ አለመሆኑ፣
- ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ ከመሰራጨቱ በፊት ጥራቱ የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉ፣
- አርሶ አደሩ ለአፈር አይነቱ ያልተመከሩ ማዳበሪያዎችን በመጠቀም ምጥን ማዳበሪያዎች በሰብል እና በአፈሩ ላይ ጉዳት እያደረሱ ያለበት ሁኔታ መኖሩ፣
- መሬት ለምነት ማጣት (የአፈር አሲዳማነት) በመጨመሩ ለአብነት በኦሮሚያ ክልል ካለው 6.01 ሚሊየን ሄክታር የሚታረስ መሬት ውስጥ ከሁለት እስከ ሦስት ሚሊየን ሄክታር የሚሆነው መሬት በአሲዳማነት መጠቃቱ እና ችግሩ ቀድሞ ከነበረበት የአገሪቱ ምዕራባዊ ክፍል ወደ ሰሜናዊና ደቡባዊ የአገሪቱ ክፍሎች እየተስፋፋ እንደሆነ እና በየአመቱ በስምንት በመቶ የምርትና ምርታማነት እድገት ለማስመዝገብ የተያዘውን እቅድ እንዳይሳካ ማነቆ መሆኑ በዚህም ምክንያት አርሶ አደሩ ቀደም ሲል ሲያመርታቸው የነበሩ ዋና ዋና ሰብሎች ከምርት ውጪ እንዲሆኑና አሲዳማነትን የሚቋቋሙ ውስን ሰብሎች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የተገደዱ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ኦሮሚያ፣ ደቡብ እና ትግራይ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና መስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡ (በናሙና ተመርጠው የታዩ ቦታዎች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡)

**የአፈር ለምነት ደረጃ እና የማዳበሪያ ፋብሪካዎችን ማቋቋምን በተመለከተ፡-**

21. ኤጀንሲው የአፈር ለምነት (Ethiosis) ደረጃ እና የማዳበሪያ አጠቃቀም ጥናት ተጠናቆ ፍኖተ ካርታው ለሶስት (አማራ፣ደቡብ እና ትግራይ) ክልሎች

አሰራጭቷል፡፡ ይሁን እንጂ

- ጥናቱ የማዳበሪያ አጠቃቀም ላይ ግልጽ የሆነ ምክረ-ኃሳብ የሚሰጥ ባለመሆኑ ጥናቱ በአጠቃላይ በናሙና የተለየ እንጂ በቀበሌ፣ በጎጥ እና በአርሶ አደር ማሳ ደረጃ ተግባራዊ በሚሆንበት መልኩ ተለይቶ የቀረበ አለመሆኑ፣
- በጥናቱ መሰረት ንጥረ ነገሮችን ከውጭ አገር በመግዛት እንደ የአካባቢው አፈር ለምነት ይዘት በተዘጋጀው የማዳበሪያ አጠቃቀም ምክረ-ሃሳብ ቀመር ምጥን ማዳበሪያዎችን አቀነባብሮ ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ታስበው የተቋቋሙ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎች አገር ውስጥ ተቀነባብሮ ከሚሸጠው ምጥን ማዳበሪያ ከውጪ ከሚገባው ጋር ሲነፃፀር በዋጋ ውድ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ማምረት አለመቻላቸው፣
- ኤጀንሲው በሰጠው ምክረ ሃሳብ መሰረት ፋብሪካውን ያቋቋሙ የገበሬዎች ኅብረት ስራ ዩኒዬኖች ማለትም በአማራ ክልል (መርከብ)፣ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል (መሊቅ)፣ በትግራይ ክልል (እንደርታ) የተባሉት ሶስት የህብረት ስራ ዩኒየኖች ለኪሳራ የተዳረጉ ሲሆን ኪሳራቸውን በዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል፡-

  - **መርከብ ህብረት ስራ ዩኒየን**
    - አገልግሎት የማይሰጥ 59 ሺ 84 ኩንታል ቦሮን፣ ዚንክ እና ፖታሽ መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ በየወሩ ለኪራይ 100 ሺ ብር ወጪ እየተደረገ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ 46 ሺ 192 ኩንታል ፖታሽ ያለጥቅም መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
    - ለወለድ 390 ሺ ብር እና ለ14 ቋሚ ሰራተኞች ያለሥራ በየወሩ 40 ሺ ብር እንዲከፍል እየተገደደ ሲሆን
  - **መሊቅ የስልጤ ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን**
    - በአግባቡ ጥናት ሳያደርግ ያስገባው 53 ሺ ኩንታል ፖታሽ ጥቅም ላይ ያልዋለ እና በመጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
    - ዩኒየኑ በየወሩ 70 ሺ ብር ለኪራይና ተጨማሪ የአስተዳደር ወጪ እንዲከፍል የተገደደ መሆኑ እና ፖታሹም የተበላሸ መሆኑ፣
    - ፋብሪካው በአግባቡ ስራውን ባመስራቱ ምክንያት በየዓመቱ 6 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ እየከሰረ መሆኑ፣
  - **እንደርታ ህብረት ስራ ዩኒየን**

- በ2006 ዓ.ም በምክረ ሃሳቡ መሰረት ከውጭ አገር ፖታሽየም ክሎራይድ፣ ቦራክስ እና ዚንክ ሰልፌት ጥሬ እቃዎችን ብር 42,529,037.33 (አርባ ሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ሰላሳ ሰባት ከ33 ሳንቲም) ወጪ በማድረግ ወደ አገር ውስጥ ቢያስገባም ጥሬ እቃዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸውና ጥቅም ላይ ሊውሉ ባለመቻላቸውና ለብልሽት መዳረጋቸው፣
- ለሌሎች ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጪዎች ብር 33,267,986.42 መዳረጉ፣
- በአጠቃላይ 75,797,023.75 ዩኒየኑ የከሰረ መሆኑ፣

- **የበቾ ወሊሶ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ**
  - የማምረት ሥራ ጀምሮ የፕሮጀክቱ አካል የነበሩ ተግባራት ያልተጠናቀቁ በመሆኑ ምጥን ማዳበሪያ የማምረት ሥራ ያቋረጠ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ህብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲዎች እና ዩኒየኖች በቀረበ መጠይቅና የመስክ ጉብኝት ወቅት ታውቋል፡፡





**ምስል1. ዩኒየኖቹ ከውጭ ያስገቡት ንጥረ ነገሮች በከፊል**



**ምስል 2. ለብልሽት የተዳረገው ንጥረ ነገር በከፊል**

22. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ አስፈፃሚ አካላት (**ዝርዝራቸው በአባሪ 3 ተያይዟል**) የምርት ማቀነባበር እና የገበያ ትስስር በተመለከተ ኤጀንሲው ስልጠናዎችን ብቻ እንደሚሰጥ፣ በአርሶ አደሮች አካባቢ የምርት ማቀነባበሪያ እንዲኖር ድጋፍ እንደማያደርግ፣ አጥንቶ የሚያመጣቸው የምርት ማቀነባበሪያ ሃሳቦች የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ የማያገናዝቡ እና የሚያቀርባቸው አዳዲስ ሃሳቦች እና የሚነድፋቸው ስልቶች የሚጀመሩ እንጂ ዘላቂነት የሌላቸው መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

23. ስለ ጉዳዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ኤጀንሲው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር መ/ቤት ያሉበት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ላይ አስተማማኝ እና በቂ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችለው እንደ ሜካናይዜሽን እና በሰብል ጥበቃ ላይ ያሉ ተግዳሮቶች ላይ እንዲሁም የዘር አጠቃቀም አጠቃላይ ማዕቀፍ ላይ የምርምር ሥራ መስራትም ሆነ በተለዩ ክፍተቶችም ቢሆን ከውጭ ቴክኖሎጂዎችን በማስገባት የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ በማድረግ የመስራት አቅሙ

ደካማ መሆኑን፣ በሌላው ዓለም የተመሰረተ እና ለሀገራችን ጠቃሚ የሆነ ቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል የድርሻውን ወስዶ መስራት ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን እንዲሁም የማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በሀገራችን እንዲኖር በተወሰደው ተነሳሽነት ውስጥ ወደ ሥራ በተገባበት ወቅት የተፈጠረውን ሰፊ ክፍተት በተለይም ቅይጥ ማዳበሪያ ዝግጅት ላይ መፍትሄ ለመስጠት የነበረውን የአቅም ክፍተት ለመሙላት አለመቻሉን እና ከዚህ አንጻር የሌሎችን ሀገሮች ተሞክሮ በማምጣት መፍትሄ ማፈላለግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

24. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የሚለው ዘርፍ ውስብስነት፣ የአርሶ አደሩ አቅም ውስንነት፣ የብዙ ባለድርሻ አካላት ጣልቃ ገብነት የሚጠይቅ መሆኑ እና ኤጀንሲው ምክረ-ሃሳብ ሰጪ እንጂ ፈፃሚ ባለመሆኑ በሌላ በኩል ኤጀንሲው የሚነድፋቸውና የሚያመጣቸው አዳዲስ ሃሳቦች ፈፃሚዎች የማይተገብሩት በመሆኑ፣ የሚነደፉ ስልቶች በሚፈለገው ደረጃ ችግሮችን ለመቅረፍ ጊዜ የሚፈልጉ በመሆናቸው እና የቢሮክራሲ/የአሰራር ችግሮች በመኖራቸው ምክንያት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እስካሁን እንደ ችግር መቀጠላቸውን ገልፀዋል፡፡

25. በተጨማሪም በግኝቱ ከተጠቀሱት ችግሮች መካከል፡-

- የግብርና ግብዓቶች በወቅቱና በበቂ መጠን አለመቅረብን በተመለከተ አብዛኞቹ ግብአቶች ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው አቅርቦታቸው በውጭ ምንዛሬ ግኝት የተመሰረተ በመሆኑ፣ ግብአቶችን በሚፈለግ መጠን የመጠቀም ሁኔታ ከምንም በላይ በእያንዳንዱ አርሶ አደር የግንዛቤ መጠንና የኦኮኖሚ አቅም ላይ የሚወሰን በመሆኑ እንደሆነ እና እነዚህ ችግሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ሊወገዱ እንደማይችሉ እና ሂደትን የሚጠይቁ በመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ ነገር ግን በኦዲት ግኝቱ የተነሱ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ ኤጀንሲው በቀጣይ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን በማካሄድ መፍትሄዎችን የማመንጨት ጥረቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል፣
- የአፈር አሲዳማነት ችግርን ለመፍታት ከኤጀንሲው የሚጠበቀው አማራጭ መፍትሄዎችን ማሳየት እንደሆነና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የአሲዳማ አፈርን በማከም የሚኖረውን የምርት እድገት የሚያሳዩ ሰርቶ ማሳያዎች በተወሰኑ አካባቢዎች በአርሶ አደር ማሳዎች ላይ እንዲካሄዱ ማድረጉን፣ የኖራ

ማምረትና ለአርሶ አደሮች ተደራሽ ማድረግን በብቃት ለማከናወን የሚያስችሉ ሞዴል አማራጮችን ለማዘጋጀት ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ጋር ስራዎች መጀመራቸው፣

- የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በአርሶ አደሩ አካባቢ በሚፈለግ ደረጃ አለመገኘት ችግርን ለመፍታት በኤጀንሲው አማካይነት የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የሜካናይዜሽን ስትራቴጂ መዘጋጀቱን ስትራቴጂውም በሜካናይዜሽን ዘርፍ የሚታዩ ማነቆዎችን በዝርዝር በመለየት የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሄዎችን ማመላከቱን፣ ኤጀንሲው በዘርፉ ለውጥ ለማምጣት አዳዲስ አሰራሮችን በፓይለት ፕሮጀክት ከሞመከር ጀምሮ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርን በመደገፍ ሰፊ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ እና የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ፕሮጀክትን በአራት ክልሎች ለመጀመር የፕሮጀክት ዲዛይን ተጠናቆ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ከጥር ወር ጀምሮ ወደ ስራ ለመግባት መታሰቡን፣
- የገጠር ፋይናንስ የአቅርቦት ጥራትን አስመልክቶ የተሰነሳውን ችግር በተመለከተ ኤጀንሲው በገጠር ፋይናንስ ስርዓት ላይ ብዙ መሰራት ያለባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን እንደሚያምን በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለማቃለል የገጠር ፋይናንስ ስትራቴጂ በመንደፍ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መቆየቱን፣
- ከ3 ዓመታት ወዲህ የግብአትና ኩፖን ስርዓት በመዘርጋት ከዚህ በፊት በተበታተነ ሁኔታ ሲሰራጭና የነበረና በወቅቱና በበቂ ሁኔታ ማዳበሪያ ያለመድረስ እንዲሁም የመክረም እና ብድር በወቅቱ ያለመመለስን ችግር በመቅረፍ ማዳበሪያ በወቅቱና በሚፈለገው መጠንና ዓይነት እንዲቀርብ፣ በብድር አመላለስ የነበረው ችግርም እንዲቀረፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉን፣
- ለአፈር ዓይነቱ ያልተመከሩ ማዳበሪያዎችን መጠቀምን በተመለከተ የኢትዮጵያ አፈር ሃብት መረጃ ስርአት ፕሮጀክት (EthioSiS) ከሀገሪቱ የእርሻ መሬቶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወካይ የአፈር ናሙናዎችን በማሰባሰብ፣ በላብራቶሪ በመመርመር፣ መረጃን በማጠናቀር እና ዘመን የደረሰበትን የዲጂታል የአፈር ካርታ ስራን በመጠቀም እስከ ወረዳ እና ቀበሌ ድረስ ያሉትን የአፈር ጠባይ ትንተና እና የማዳበሪያ ምክረ ሃሳብ የመስጠትን ስርዓት በመዘርጋት እንደ ሃገር ብሎም ለአፍሪካ አገራት ተምሳሌት የሆነ

ፕሮጀክት እንደሆነ ነገር ግን አሁን ባለበት ምዕራፍ በተለይ በአርሶ አደር ማሳ ደረጃ የማዳበሪያ ምክረ ሃሳብን በተሟላ መልኩ ለመስጠት እንዲችል ሆኖ በዲዛይን ደረጃ አለመቀረጹን፣ ፕሮጀክቱ በአሁኑ ወቅት ያቀዳቸውን ግቦች አሳክቶ በመጠናቀቅ ሂደት ላይ እንደሚገኝ፣

- የማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች አስመልክቶ የተነሱ ችግሮች እንዲፈቱ የሚመለከታቸው አካላት ድርሻቸውን ሊወጡ የሚገባ እንደሆነ እና የተከሰቱት ችግሮች የኤጀንሲው ሃላፊነት ተደርገው መወሰድ እንደሌለባቸው፣
- የግብርና የምርት ማቀነባበሪያን ማስተዋወቅና የምርት ማቀነባበርን አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እና የባለድርሻ አካላት ምክክር በማድረግ፣ የድርጊት መርሃ ግብር ማዕደቅ የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት መጀመር ጋር እንዲሁም የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር ኢኒሼቲቭ በኤጀንሲው በመጀመሩ በዘርፉ ታቅደው የነበሩት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች አፈፃፀም በእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ ተስፋፍተው እንዲካተቱ መደረጉን፣ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/፣ በቃለ መጠይቅ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

26. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ ተግዳሮት ናቸው ብሎ የገለፃቸው እንዲፈቱ ጥረት ማድረጉን የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡ፣
- በቅድሚያ ችግሮች እንዳይከሰቱ ስልቱ ቀጣይነት ባለውና ሊተገበር በሚችል መልኩ ሊዘጋጅ ይገባ የነበረ በመሆኑ፣
- የፈፃሚዎችን የአቅም ውስንነት በቅድሚያ ለይቶ በማወቅ አቅማቸው ሊጎለብት የሚችልበትን አቅጣጫ የማሳየት ጥረቱ በየጊዜው ማከናወን የነበረበት በመሆኑና
- በግሉም ሆነ ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራቱን የገለፃቸው ተግባራትን በተመለከተ ማስረጃ ባለማቅረቡ፣

የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

27. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ጥናቶችና የሚነድፋቸው ስልቶች ወደ አርሶ አደሩ ወርደው ተግባራዊ አለመደረጋቸው እና በራሱ ስልቶች ላይ ችግሮች የሚገጥሙት መሆኑ ኤጀንሲው ሲቋቋም በዘርፉ ያሉትን ችግሮች በመለየት ማነቆዎችን ለመፍታት በመሆኑ እራሱ ሌሎች ማነቆዎችን

በመፍጠር በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ በተፋጠነ መልኩ እንዳይከናወን እና ሊደረስ የታሰበው ግብ እንዳይመታ ያደርገዋል፡፡

**ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ጥናቶች ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እና ተግባራዊ መሆናቸውን በተመለከተ፡-**

28. በኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች የአርሶ አደሩን እና የአስፈፃሚ አካላትን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ እና ሊተገበሩ የሚችሉ ሊሆኑ፤ጥናቶቹ ተግባራዊ መደረጋቸውን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ሊከታተል ይገባል፡፡

29. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ጥናት ቢያደርግም ጥናቶቹ፡-

- የአነስተኛ  አርሶ አደሩን እና የፈፃሚዎችን ፍላጎት እና አቅም መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣ ለዚህም ማሳያ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ፕሮጀክት እ.አ.አ ሚያዝያ 2016 ተጀምሮ መጋቢት 2018 መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም ፕሮጀክቱን ለመጀመር ስትራቴጂ ተቀርጾ ነገር ግን የአርሶ አደሩን አቅም ያላገናዘበ እና አርሶ አደሩ አቅሙን ለማጎልበት የሚያስችል ሌሎች አማራጮች ባለመኖራቸው  ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑ፣ እንዲሁም
- ኤጀንሲው ያከናወናቸው ጥናቶች እና ምክረ ሀሳቦች በሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ጥናቶቹና ምክረ ሀሳቦቹም በሚመለከታቸው ተቋማት/ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የፌዴራልና የክልል ህብረት ሥራ ኤጀንሲዎችና ማህበራት፣ የክልል ግብርና ቢሮዎች ያልተተገበሩ መሆናቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብርና ተቋማት ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. በናሙና ተመርጠው የታዩ አስፈፃሚ አካላት የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የሰብል ምርትና ምርታማነትን በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶችን እንደሚያደርግ ነገር ግን  ጥናቶቹን ወደ መሬት ለማውረድ ችግር ያለባቸው መሆናቸውን፣ጥናቶችን በአማካሪ ድርጅቶች የሚያስጠና በመሆኑ አጥኚው ድርጅት እስከታች ድረስ ወርዶ ችግሮችን በጥልቀት አለማየት ችግሮች መኖራቸውን እና በየጊዜው በሚከናወኑ ጥናቶች ዙሪያ ከአስፈፃሚ አካላት ጋር ተወያይቶ የጋራ አድርጎ ያለመስራት ችግሮች እንዳሉበት ገልፀዋል፡፡

31. ስለሁኔታው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በግብርና ሜካናይዜሽን ሥራ ሀገራችን የሞት ሽረት እንቅስቃሴ በማድረግ ሜካናይዝድ የሆነ አሰራር ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ማሰባሰብ ተግባራዊ ለማድረግ በምታደርገው ውስን እንቅስቃሴ እንዳለ ሆኖ ለሀገራችን የግብርና ዕድገት ከፍተኛ ማነቆ ሆኖ የቆየውንና እስከሁንም ድረስ ተግዳሮት የሆነውን ጉዳይ ኤጀንሲው ሚ/ር መ/ቤቱ መፍትሄ በመስጠት ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ለማሸጋገር እያደረገ ያለውን ጥረት በተገቢው መጠን መደገፍ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

32. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ሊደግፍ የሚችል ምክረ-ሃሳብ እንደሚሰጥ፣ ምክረ-ሃሳቦች በመተግበር ዙሪያ የአርሶ አደሩን አቅም ማዕከል አድርጎ እንደሚሰራ ማለትም ከአርሶ አደሩ የመግዛት አቅም በላይ ለሆኑ ምክረ ሃሳቦች የብድር አቅርቦት እንዲመቻች እንደሚያደርግ፣
- በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ ችግሮች ሙሉ በሙሉ መቅረፍ እንደማይቻል፣
- የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ (የተፈጥሮ፣ የገንዘብ እና አሰራር ስርዓት)፣ የፈፃሚዎች አቀባበልና ጥናቶቹን እንደተዘጋጁ በቀላሉ ለመተግበር አስቸጋሪ በመሆናቸው እንደሆነ፤
- የሚያከናውናቸው ጥናቶች በተመለከተ ደግሞ ፈፃሚ አካላት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋው ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ክትትል ማድረግ የማይችል በመሆኑ፣
- ከግብርና ሜካናይዜሽን ፓይለት ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ የተነሳው ችግር በተመለከተ ፕሮጀክቱ በ2015 እና 2016 በደቡብ ክልል በላንፋሮና ሌሞ ወረዳዎች ስራ ጀምሮ እንደነበርና በገጠሙ ተግዳሮት ምክንያት እንደገና እንዲጠና በማስፈለጉ እና በተሻለ አቀራረብ እንዲፈፀም በመታሰቡ እንዲቆም እንደተረገ ነገር ግን በአሁኑ ሰአት የተባሉትን ተግዳሮቶች መፍታት የሚያስችል የፕሮጀክት ንድፍ የተጠናቀቀ በመሆኑ በአዲስ መልክ ከጥር ወር 2010 ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን፣
- ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ጥናቶች በፈፃሚ አካላት ወደ ተግባር እንዲገቡ ጥረት የሚያደርገውም ፈፃሚ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ዝርዝር ዕቅዶች በሚያዘጋጁበት ጊዜ በጥናት ሰነዶችና በስትራቴጂዎች የተቀመጡ ምክረ ሃሳቦች

በመነሻነት እንዲገለገሉ በማገዝ እንደሆነ፣

ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/ እና በቃለ መጠይቅ በሰጡት አስተያየት ገልፀዋል፡፡

33. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ

- ኤጀንሲው በጥናቶች ተግባራዊነት ላይ የአርሶ አደሩን አቅም ለማጎልበት ያከናወናቸው ተግባሮች ማስረጃ ባለማቅረቡ፣
- ጥናቶቹ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ቀድሞ መተንበይና የፈፃሚዎች አመለካከት ላይ መስራት የነበረበት በመሆኑ፣
- የሚከናወኑት ጥናቶቹ ችግሮቹን የሚፈቱና ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን የነበረበት በመሆኑ፣
- የግብርና ሜካናይዜሽን ፓይለት ፕሮጀክት ሲጠና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ከግንዛቤ ማስገባት የነበረበት በመሆኑ እና
- ፈፃሚ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ዝርዝር ዕቅዶች በሚያዘጋጁበት ጊዜ በጥናት ሰነዶችና በስትራቴጂዎች የተቀመጡ ምክረ ሃሳቦች በመነሻነት እንዲገለገሉ እገዛ ማድረጉን የሚያሳይ ማስረጃዎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለማቅረቡ

የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

33. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚነድፋቸው ስልቶች ሊተገበሩ የሚችሉ አለመሆናቸው እንዲሁም በፈፃሚ አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ በጥናቶቹ አማካይነት በዘርፉ ሊመጣ የታሰበው ውጤት እንዳይመጣ ከማድረጉም ባሻገር ጥናቱን ለማካሄድ የወጣው ጊዜ እና ገንዘብ  እንዲባክን አድርጓል፡፡

**ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው ቦታዎች ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ማዘጋጀቱን እና  ክልሎች የተመደበላቸው በጀት እንዲያውቁት መደረጉን በተመለከተ፡-**

34. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ በኃላፊነት የሚመራቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ቦታ (ክልል፣ዞን እና ወረዳ) የሚመርጥበት ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ሊያዘጋጅ እና በመስፈርቱ መሰረት ቦታዎቹ ሊመረጡ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ክልሎች የተመደበላቸውን በጀት እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ፡-

**ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉበት ቦታ የሚመረጥበት መስፈርት በተመለከተ፣**

- ኤጀንሲው ከቀጥታ ዘር ግብይት በስተቀር ሌሎች ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ቦታዎች (ክልል፣ ዞን እና ወረዳ) የመረጠበትን መስፈርት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ ሲሆን ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ከሚያደርግባቸው ክልሎች ጋር ሳይገናኝ በቀጥታ በወረዳዎች ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑ፣

**ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ለሚደረጉባቸው ለእያንዳንዱ ክልል የተመደበውን በጀት ማሳወቅን በተመለከተ፣**

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በጀት በተመለከተ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረግባቸው እያንዳንዳቸው ክልሎች/ወረዳዎች ስለተመደበላቸው በጀት እና ስለ ፕሮጀክቱ ዝርዝር ተግባራት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ፣

36. ይህን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው የታዩ (የኦሮሚያ፣ የደቡብና የትግራይ) ክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ/ጽ/ቤትና ህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ከአስፈፃሚ አካላት ጋር በጋራ ለይቶ የመተግበር ችግር እንዳለበት ማለትም ከቢሮዎች እውቅና ውጭ በራሱ ፕሮጀክቶችን እንደሚተገብር እንዲሁም ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ሲተገብር ቢሮዎችን ቀርቦ እንደማያማክር እና ለፕሮጀክቶች የሚደረገው ወጪ መጠንም በግልፅ እንደማያሳውቅ ገልፀዋል፡፡

37. ስለ ሁኔታው ኤጀንሲው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/ እና ለረቂቅ ሪፖርት በሰጠው ምላሽ በኤጀንሲው ፕሮጀክቶች ሲቀረጹ የሚተገበሩበት አካባቢ እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ መስፈርቶቹም እንደሚለያይ ነገር ግን የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር በመጠቀም የትኛው ወረዳ ለየትኛው ኮሞዲቲ አቅም እንዳለው በመረጃ በመደገፍ የሚለይበት አሰራር መተግበሩን፣ በዚህም ሂደት ከፌዴራል እስከ ወረዳ ያሉ አካላት እንደሚሳተፉ እንደሚያደርግ፣ ፕሮጀክቶች ከመተግበራቸው በፊት የጥናት ሰነዳቸውና ዝርዝር ጉዳዮች /ዓላማ፣ ግብ፣ በጀት/ በባለድርሻ አካላት በአውደጥናቶች ተተችቶባቸው ወደ ስራ እንዲገቡ እንደሚደረግ፤ የፕሮጀክቶች ወጪን በተመለከተ አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች በርካታ ወረዳዎችን የሚሸፍኑ በመሆናቸው

የፕሮጀክቱ በጀት በጥቅል እንደሚታቀድ በየወረዳው ለመለያየት የሚያስቸግር መሆኑን ነገር ግን በቀጣይ ጥቅል የፕሮጀክቶች በጀት ወረዳዎችና ክልሎች እንዲያውቁት ከቀድሞው በተሻለ መልኩ አጠናክሮ እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

38. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከክላስተሪንግ ውጪ እንደ ፕሮጀክቶቹ ዓይነት የተጠቀመባቸውን መስፈርቶች እና በባለድርሻ አካላት በመተቸት ወደ ስራ የገቡ የፕሮጀክቶች ጥናት ሰነዶች ማስረጃዎችን ባለማቅረቡ እንዲሁም በናሙና የታዩ ፕሮጀክቶቹ የሚገኙባቸው ክልሎችም ሆነ ወረዳዎቹ ስለፕሮጀክቱ እንደማያውቁ በመግለጻቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

39. ኤጀንሲው እያንዳንዱን ፕሮጀክት ተግባራዊ የሚያደርግበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግልፅ ወጥ የሆነ መምረጫ መስፈርት አለማስቀመጡ፣ በያንዳንዱ ወረዳ ለሚተገበረው ፕሮጀክት የወጣው በጀት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ለሚደረግበት ክልል/ወረዳ አለማሳወቁ አሰራሩ ግልፅነት እንዲጎድለውና ከታለመለት አላማ ውጪ እንዲውል መንገድ ሊከፍት የሚችል፣ በፈፃሚዎች ዘንድ ተአማኒነትን እንዲያጣ እና የፕሮጀክቱን ዝርዝር ተግባራትን በማሳወቅ በጋራ አለመፈጸሙ የፕሮጀክቱ ባለቤት የሆኑ ፈጻሚ አካላት ፕሮጀክቶችን ተረክበው ለማስቀጠል እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የሚመራቸው ፕሮጀክቶች ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች ማለፋቸውን በተመለከተ፣**

40. ኤጀንሲው የሚመራቸው ማንኛውም ፕሮጀክቶች፤ በፕሮጀክት እቅድ፣ ትግበራ፣ አመራር፣ ግምገማና የመማማር ሂደት መመሪያ (project planning, implementation, monitoring, evaluation and learning process guideline) ላይ የተቀመጡትን የትግበራ ቅድመ-ዝግጅት (Implementation set-up) ሙከራና ማሻሻያ (testing and refinement) እና ማስረከብ (handover) ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች እንዲያልፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ለኦዲቱ በናሙና የተመረጡት የግብርና ግብአት መከታተያ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የቀጥታ ዘር ግብይት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት፣ የግብርና አገልግሎት ማዕከል፣ ሞዴል የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል አቅም ግንባታ፣ የግብአት ኩፖን ሽያጭ እና አውቶሜት ኢ-ቫውቸር ሲስተም እና

የምጥን ማዳበሪያ ፕሮጀክቶች ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎች ማለፋቸውን የሚሳይ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ አልቀረበም፡፡

42. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ (ዝርዝራቸው በአባሪ 3 ተያይዞዋል፡፡) የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤት እና ህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሃላፊዎች በክልላቸው በሚገኙ ወረዳዎች ኤጀንሲው ተግባራዊ እያደረጋቸው ያሉ ፕሮጀክቶች ሶስቱን የትግበራ ደረጃዎችን የሚያልፉ መሆናቸውን እንደማያውቁ ገልፀዋል፡፡

43. ስለ ሁኔታው የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የትግበራ ቅድመ ዝግጅት ጋር ተያይዞ ማንኛውም ፕሮጀክት ቴምፕሌት እና ዲዛይን እንዳለው፣ ሙከራና ማሻሻያ በተመለከተ ተሞክሮ ማሻሻያ የተደረገበት (ሪፋይን) የተደረገ ፕሮጀክት አለመኖሩን፣ ርክክብ ሂደትን በተመለከተ በአሁኑ ወቅት የተሟላ የፕሮጀክቶች ማጠቃለያና የርክክብ ሰነድ የሚዘጋጅበትን ስርዓት በመፍጠር ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ጭምር በማካተት የተሟላ ስራ ለማካሄድ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Factsheet/ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

44. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የፕሮጀክቶች የቅድመ ዝግጅት ቴምፕሌትና ማስረጃ ባለመቅረቡ የፕሮጀክቶች ርክክብ ሂደትን አስመልክቶ የቀረበው ማስረጃም በረቂቅ ደረጃ ላይ ያለ እንጂ ወደ ተግባር የተገባበት ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

45. ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን ሶስት የትግበራ ደረጃዎችን እንዲያልፉ አለማደረጉ ፕሮጀክቶቹ ያሉበት ደረጃ በወቅቱ እንዳይታወቅ እና የመፍትሄ እርምጃ እንዳይወሰድ ከማድረጉም በላይ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ የጊዜ እና የገንዘብ ወጪ ከተደረገባቸው በኋላ እንዲቋረጡ በማድረግ የሀገሪቷ ውስን ሀብት እንዲባክን ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚጠናቀቁ ስለመሆኑ፣**

46. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የረጅም ጊዜ ተግባር ባለቤት (deliverable owner) የስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

47. በኦዲቱ ወቅት ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በአራቱ (ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣አማራና ትግራይ) ክልሎች ስር በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ከሚተገበራቸው ፕሮጀክቶች በናሙና ተመርጠው የታዩት፡-

➢ **የግብርና ግብዓት መከታተያ ፕሮጀክቱ** እቅድ ዲዛይኑ ጥቅምት 2009 ዓ.ም (እ.አ.አ ኦክቶበር 2016) ኢንኩቤሽኑ ታህሳስ 2010 ዓ.ም. (ዲሴምበር 2017) ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታየው በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በስልጤ ዞን ስልጢ ወረዳ ከፕሮጀክት ዲዛይን ጊዜው በፊት በ2008 ዓ.ም የካቲት አካባቢ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የተቋረጠ መሆኑ፣

➢ **የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ፓይለት ፕሮጀክትን** ሚያዚያ 2008 ( አፕሪል 2016) ጀምሮ መጋቢት 20100.ም (ማርች 2018 ለማጠናቀቅ አቅዶ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ወደ ተግባር አለመግባቱ፣ ይህን ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ ከአቀዳቸው ወረዳዎች በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ በታየው በደቡብ ክልል ሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ ሆሳዕና ከተማ ላይ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

➢ **የቀጥታ ዘር ግብይት ፕሮጀክት** እ.አ.አ ታህሳስ 2014 ተጀምሮ መጋቢት 2017 መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በሲዳማ ዞን ሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ገና በመስከረም 2010 ዓ.ም በጅምር ላይ ያለ ሲሆን በትግራይ ክልል እንደርታ ወረዳ ደግሞ የተቋረጠ መሆኑ፣

➢ **የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት ፕሮጀክት** እ.አ.አ 2007 ዓ.ም ተጀምሮ 2012 ዓ.ም መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታየው በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን አንገጫ ወረዳ ዶዮ ገና ከተማ የሚገኘው የዘርታ ከምባታ ዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየን በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ እና ሰልፍ ሄልፕ አፍሪካ ከሚባል ድርጅት በተገኘ ብር 299,786.19 ድጋፍ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም የላቦራቶሪ እቃዎችና ባለሙያ እንዲኖረው አለመደረጉ፣ ፕሮጀክቱ ቢዝነስ ዕቅድ፣ ግምገማና የማስፋፊያ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፣ የዘርታ ከምባታ ዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየን የመጋዘን ችግር ያለበት ሲሆን ዘሮቹ ምቹ ባልሆነ ቦታ ተቀምጠው ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑ፣ በኤጀንሲው አማካይነት በሰልፍ ሄልፕ አፍሪካ የሚካሄደው የመጋዘን ግንባታ

በቁፋሮ ደረጃ ላይ ብቻ ሲሆን በታቀደውና በውሉ መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ፣



**ምስል 3. ምቹ ያልሆነው የዘር ማከማቻ በዘርታ ከምባታ ዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየን**



**ምስል 4. በቁፋሮ ደረጃ ብቻ ያለው የዘርታ ከምባታ ዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየን የመጋዘን ግንባታ**

- **የግብርና አገልግሎት ማእከል ግንባታ ፕሮጀክትን ኤጀንሲው ከዩ.ኤስ.ኤድ ባገኘው** ድጋፍ እ.ኢ.አ ሐምሌ 2015- ሚያዝያ 2018 ድረስ ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደው ፕሮጀክት ሲሆን በናሙና ተመርጠው ከታዩ ወረዳዎች ውስጥ ከኦሮሚያ ክልል የወሊሶ፣ ከደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል የሆሳዕና ግብርና አገልግሎት ማዕከል ፕሮጀክቶች በ2009 ዓ.ም ስራ የጀመሩ ቢሆንም ፡-
    - ✓ ማዕከላቱ ከቀጥታ የዘር ግብይት ፕሮጀክት ጋር ትስስር ያልፈጠሩ፣

- ✓ ለአርሶ አደሩ ግብዓቶችን የሚያቀርቡት ከግል ነጋዴዎች በፕሮፎርማ በመግዛት በመሆኑ ፕሮፎርማው የሚወስደው ጊዜ ረዘም ያለ ስለሆነ አርሶ አደሩ ግብአት በወቅቱ እንዳያገኝ ማድረጉ፣
- ✓ የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርታማነት እንዲጨምር በቴክኖሎጂ በኩል የተጀመረ ስራ አለመኖሩ፣
- ✓ የተሻሻሉ ፀረ-አረሞች ከገበያ በመጥፋታቸው ፀረ-አረሞችን በብቃትና በጥራት እያቀረቡ አለመሆኑ፣በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ድጋፍ የሚቀርብላቸው ብቃትና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ- አረም አለመኖሩ፣
- ✓ የግብርና ሜካናይዜሽን የአቅርቦት ሰንሰለት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል አለመኖሩ፣
- ✓ የግብርና ግብዓትን ጅምላ ንግድ ከሚያከናውኑ ዩኒዬኖች እና ከግብርና ፌዴሬሽን ጋር አለመተሳሰራቸው፣
- ✓ የማዕከላቱ ውጤታማነት እንዲረጋገጥ የመምራት፣ የማሰልጠን እና የክትትል ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፣
- ✓ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ማቋቋሚያ ቦታዎች የቅድመ አካባቢ ጥናት ምርምራ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳ ጥናት አለመካሄዱ፣
- ✓ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት በተቀመጠው መስፈርት ማለትም (ቦታው ፍሳሽን ለማስወገድ አመቺ በሆነ አቅጣጫ ላይ የተቀመጠ፣ ግድግዳዎቹ ኬሚካልና ሌላ ፍሳሽን ሊከላከሉ የሚችሉ፣ጭስ ማውጫ ያለው፣ ወለሉ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል፣ በቂ አየር እና ብርሃን ሊያስገባ የሚችል ወዘተ..) በማሟላት ያልተገነቡ መሆናቸው፣
- ✓ በሚፈለገው የሰው ሃይል ያልተሟሉ መሆኑ፣ የግብአት ፍላጎትና አቅርቦት ዳሰሳ አለመደረጉ፣ መተዋወቅ ያለባቸው ቴክኖሎጂዎች እንዲለዩ እና እንዲተዋወቁ አለመደረጋቸው፣
- ➢ በአቅራቢያቸው ካሉ ቀበሌ ሳተላይት ሱቆች ጋር ያልተሳሰሩ እና የገበያ መር የግብርና ምክረ ኃሳብ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ➢ የእንስሳት መድኃኒት ግዢ ጋር ተያይዞ መመሪያ ባለመኖሩ በምትኩ የሰብል ግዢ መመሪያን እየተጠቀሙ መሆኑ፣
- ➢ ማዕከላቱ ለሚያካትቷቸው ግብዓቶች፣ ቴክኖሎጂዎች እና አገልግሎቶች ሰርቶ ማሳያ እና መስክ ምልከታ ያልተደረገ ሲሆን በደቡብ ክልል ሃዋሳ ከተማ ሰርቶ

ማሳያውን ጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም ተጀምሮ መጋቢት 2010 ዓ.ም ለማጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም እስከ መስከረም 2010 ዓ.ም ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፣

- **የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል አቅም ግንባታ ፕሮጀክት** መጋቢት 2008 ዓ.ም (ማርች 2016) ተጀምሮ መጋቢት 2010 ዓ.ም. (ማርች 2018) መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታየው በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ቶሌ ወረዳ ስራ ለመጀመር በሚያዝያ ወር 2008 ዓ.ም ሳይት መረጣ የተደረገ ቢሆንም የተከናወኑ ስራዎች አለመኖራቸው፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ኦክስፋም በተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አማካይነት በክልሉ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ 12 ሚሊየን ብር ተመድቦ ስራው እንዲሰራ ታስቦ የነበረ ቢሆንም ድርጅቱ በክልሉ ስራውን ሳያከናውን ለደቡብ ክልል ልማት ማህበር ያስረከበው ቢሆንም ማህበሩ ከተቋሙ ሲረከበው የተሰጠው በጀት በቂ ባለመሆኑ የፕሮጀክቱን ስራዎች ማስቀጠል አለመቻሉን የደቡብ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ ከሰጠው ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- **የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ማቋቋም ፕሮጀክት** እ.ኢ.አ በ2012 ተጀምሮ በ2015 ተጠናቆ ማምረት እንደሚጀምር በኤጀንሲው የታቀደ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ፡-
    - በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው የበቾ ወሊሶ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ፡-
        - ✓ በ2006 ዓ.ም ተመርቆ በ2007 ዓ.ም የማምረት ስራ የጀመረ ቢሆንም የፕሮጀክቱ አካል የሆኑ ተግባራት ማለትም መጋዝን ግንባታ በኤጀንሲው ብር 3,028,756 ድጋፍ በ30/1/2008 ዓ.ም ተለቆ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም አለመጠናቀቁ፣
        - ✓ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ለፋብሪካው ተገዝቶ በ12/14/2015 የቀረበ የላቦራቶሪ ዕቃዎች ቢኖሩም ባለሙያ በመቅጠር እንዲጀምሩ አለመደረጉ፣
        - ✓ ኬሚካሎችን ለማዋሃድ የሚያገለግል (Relitech) መሳሪያ ተገዝቶ የቀረበ ቢሆንም አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣
        - ✓ የፋብሪካው ፍሳሽ ማስወገጃ ማሽን ተገዝቶ ሞተር ባለመገጠሙ እስካሁን ስራ ላይ አለመዋሉ፣ ከፋብሪካው የሚወጣ ተረፈ ምርት ማስወገጃ ቦታ ባለመኖሩ ፋብሪካው ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን 900 ኩንታል የሚሆን ተረፈ ምርት ፋብሪካው ውስጥ ተከማችቶ ያለመሆኑ፣

- ✓ ለፋብሪካው ተገዝተው ስራ የጀመሩ ማሽኖች በየጊዜው የሚበላሹ መሆናቸው፤
- ✓ ለፕሮጀክቱ ምርት ማሳያ የተመረጠ የገበሬዎች የስልጠና ማዕከል ያልተለየ መሆኑ፣ ለሰርቶ ማሳያ ተግባራት ለልማት ጣቢያ ሰራተኞችና ለሚተገብሩ አርሶ አደሮች የተሰጠ ስልጠና፣ ለሰርቶ ማሳያ ወደ ማዕከላት የተሰራጨ ማዳበሪያ እና ከሰርቶ ማሳያው የተሰበሰበ መረጃና የተሰጠ ትንታኔ አለመኖሩ፣
- ✓ ዩኒዬኑ ግብዓት በራሱ ስለማይገዛና መንግስት ስለሚያቀርብ በኤጀንሲው የግብዓት ቲም ከባንክ ብድር እንዲያገኝ ያልተመቻቸለት መሆኑ፣ለህብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬኑ የተዘጋጀ የንግድ ስራ ዕቅድ አለመኖሩ፣



**ምስል 5. ግንባታው ተጀምሮ ያልተጠናቀቀው የበቾ ወሊሶ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ መጋዘን ግንባታ**



**ምስል 4 የበቾ ወሊሶ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ተገዝተው የቀረቡና ያለአገልግሎት የተቀመጡ የላብራቶሪ መሳሪያዎች፤**



**ምስል 5 በበቾ ወሊሶ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ማስወገጃ አጥቶ ተከማችቶ የሚገኘው 900 ኩንታል ተረፈ ምርት**

- በደቡብ ክልል ስልጤ ዞን የሚገኘው የመሊቅ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ በ2008 ዓ.ም ማምረት ቢጀምርም በ2009/10 ምርት ዘመን ማምረት ያቆመ፣ የተገነባው ፋብሪካ ለዩኒየኑ እንደ መጋዝን እያገለገለ፣ ለፋብሪካው የተቀጠሩ ሰራተኞች ስራ የሌላቸው በመሆኑ በዩኒየኑ ሌላ ስራ ላይ ተመድበው እየሰሩ፣ ለፋብሪካው ሊገነባ የታሰበው መጋዝን ግንባታው ያልተጠናቀቀ መሆኑ እና ሌሎች የፕሮጀክቱ አካል የሆኑ ስራዎች ያልተጠናቀቁ መሆናቸው፣



**ምስል 6 የመሊቅ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካው ማምረት ያቆመ መሆኑን የሚያሳይ ምስል**



**ምስል 7 ለመሊቅ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካነት የታሰበው ለዩኒየኑ እንደ መጋዘን እያገለገለ መሆኑን የሚያሳይ**

- በትግራይ ክልል የሚገኘው የእንደርታ ምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታው ተጠናቅቆ 2007 ዓ/ም ስራ የጀመረ ቢሆንም፡-
    - ✓ ስለ ፋብሪካው እውቀት ያለው ማናጀር ያልተቀጠረለት፣የንግድ ማማከርና የንግድ ስራ እቅድ ያልተሰራለት፣የኦፕሬሽናል፣የአስተዳደርና የቴክኒክ ስልጠና እና የትግበራ ድጋፍና ክትትል ያልተደረገለት፣
    - ✓ የሚያመርተውን ማዳበሪያ ከገበያ ጋር የማስተሳሰር ውስንነት ያለበት ሲሆን በዚህ ምክንያት 425 ኩንታል ከፍላጎት በላይ ተመርቶ በመጋዘን ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
    - ✓ ፋብሪካው ደስት አብዞርቨር እና የተረፈ-ምርት (ዌስቴጅ) ማከማቻ ቦታ የሌለው፣ የሰራተኛ ሴፍቲ መጠበቂያ፣ የላብራቶሪ እቃዎች የተገዙ ቢሆንም

ያልተተከሉ (not installed) እና የላብራቶሪ ባለሙያ ያልተቀጠረለት መሆኑ፣



**ምስል 7 በመጋዘን ተከማችቶ የሚገኘው ማዳበሪያ**

➢ የህብረት ስራ ማህበራት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት እ.ኢ.አ ፕሮጀክቱ እንደ ሙከራ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል በሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት ሙከራ ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል ተጀምሮ በእስኬል አፕ ደረጃ ላይ ሳይደርስ የተቋረጠ ሲሆን በትግራይ ክልል ግን ያልተጀመረ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በመስክ በተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ (ዝርዝራቸው በአባሪ 3 ተያይዞዋል፡፡) የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች /ጽ/ቤት እና ህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሃላፊዎች ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ያስረከባቸው ፕሮጀክት አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

49. ስለ ሁኔታው የኤጀንሲው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ

- የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ በአሁኑ ጊዜ ባለድርሻ አካላት እየተወዛገቡበት ያለ ጉዳይ እንደሆነ ይህም ሊከለሰት የቻለው የግብርና ሚኒስቴር ዩኒየኖቹ አቅም ስላላቸው በራሳቸው ማስቀጠል የሚችሉ በመሆናቸው ኤጀንሲው አስረክቦ እንዲወጣ በመገለፁ ምክንያት  እንደሆነ፣

- የግብርና ግብአት መከታተያ በሙከራ (pilot) ተጀምሮ በሙከራው የተፈለገው ውጤት ላይ ሊደረስ ባለመቻሉ ሊቋረጥ መቻሉን፣
- የግብርና ሜካናይዜሽን በተመለከተ በአራቱ ክልሎች ሜካናይዜሽን ማዕከል ለማቋቋም ሊዝ ፋይናንሲንግ ከብሄራዊ ባንክ በወቅቱ ባለመለቀቁ፣
- የቀጥታ ዘር ግብይት (redesign) ክለሳ የሚያስፈልገው በመሆኑ፣
- የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ብዜት በኦዲቱ በናሙና ተመርጦ የታየው የዘርታ ከምባታ ዩኒየን የቢዝነስ እቅድ ግምገማና ማስፋፊያ እቅድ አለመኖር በተመለከተ በፕሮጀክቱ ባለሙያዎችና በክልሉ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ድጋፍ የ5 ዓመት የቢዝነስ እቅድ በ2008 እንደተሰራለት፣ በ2009 ዓ.ም ይህንኑን የቢዝነስ እቅድ አሻሽሎ መስራቱን፣ በዚህም መሰረት በ2009 2,388 ኩንታል የተጣራ ዘር አምርቶና አዘጋጅቶ መሸጡን በ2010 ዓ.ም እቅዱን በማሳደግ 10,248 ኩ/ል ወደ ገበያ ለማስገባት እየሰራ እንደሚገኝ፣
- የ5 ዓመት የቢዝነስ እና ማስፋፊያ እቅድ እንዲሁም ዓመታዊ እንዲሁም ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ከዩኒየኑ ማግኘት እንደሚቻል፣ የዩኒየኑ የመጋዘን ግንባታ ሊዘገይ የቻለበትም ምክንያት ግንባታው የሚከናወነው በየወቅቱ ከተለያዩ አካላት ፋይናንስ በማፈላለግ እንደሆነና የሚያስፈልገው ፋይናንስም የተገኘው መጋቢት 2009 በመሆኑ ሊዘገይ መቻሉን በአሁኑ ሰዓት የኮለን ስራዎችን አጠናቆ የብሎኬት ድርደራና የጣራ ስራዎችን ለመስራት በዝግጅት ላይ እንደሆነና ስራውም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ፣
- የገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም አቅም ግንባታ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚደረግበት ኦሮሚያ ክልል ቶሌ ወረዳ ከኤጀንሲው ውል ወስዶ ማእከሉን በመስራት ላይ የነበረው ኦክስፋም አሜሪካ የሚበል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ቀደም ሲል ተከስቶ በነበረው ያለመረጋጋት ችግር ምክንያት ስራዎቹ እንደዘገዩ በአሁን ጊዜ ግን የተፈጠረውን ክፍተት የሚያካክስ የተፋጠነ አዲስ እቅድ አዘጋጅቶ ማቅረቡንና ያለ ተጨማሪ በጀት የጊዜ ማራዘሚያ በመፍቀድ ስራዎች እንዲጠናቀቁ አስፈላጊው ክትትል እንደሚደረግ፣
- የደቡብ ክልል ማሰልጠኛ ማዕከል በግንባታ ዙሪያ በበጀት ውስንነት ምክንያት በሲሚንቶ ሁሉንም ግንባታዎች መስራት ባለመቻሉ በአካባቢ በሚገኝ ቁሳቁስ መስራት ሲጀመር የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ስራው እንዲቋረጥ በማድረጉ የተወሰነ መዘግየት መከሰቱ፣

- የህብረት ስራ ማህበራት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት በአራት ክልሎች ( ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ትግራይ) ለሁለት አመታት በተመረጡት አቅም ገንቢዎች የአቅም ግንባታ ስራው ተሰርቶ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም መጠናቀቁ፣ የፕሮጀክት መዝጊያ ደብዳቤ ለአቅም ገንቢዎች እንደተሰጠ እና የፕሮጀክቱን አጠቃላይ አፈፃፀም (terminal evaluation) ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ፣
- የግብርና አገልግሎት ማዕከል ኤጀንሲው ከለጋሹ ጋር የተፈራረመው ፈንድ ስላልተለቀቀለት ሊጀመር አለመቻሉን

ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Factsheet/ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

50. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በኤጀንሲው የሚነደፉ ፕሮጀክቶች ሊያገጥሙዋቸው የሚችሉ ችግሮችን ቀድሞ መተንበይ የነበረበት በመሆኑ፣ ችግሮችም ሲከሰቱ ወቅታዊ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ ስለነበረበት እና ፕሮጀክቶቹ በታቀደላቸው ጊዜ እንዳይከናወኑ አድርጎአቸዋል ብሎ ያቀረባቸው ምክንያቶች በትክክል የተከሰቱ መሆናቸውን እና ለችግሩ ተወሰደ የተባለው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲሁም ማዳበሪያዎቹንም በተመለከተ ግብርና ሚኒስቴር ለዩኒዮኖቹ እንዲያስረክብ የታዘዘበት ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

51. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚነድፋቸውን ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የረጅም ጊዜ ባለቤት አለማስተላለፉ በፕሮጀክቶቹ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው አነስተኛ አርሶ አደሮች በወቅቱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ ፕሮጀክቶቹ ለግብርናው ማነቆ የሆኑ ችግሮች ለመፍታት እንደመነደፋቸው መጠን አገሪቱ በዘርፉ ልትደርስ/ ልታስመዘግብ ያቀደችውን ዕቅድ እንዳታሳካ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው ወደ ተግባር ባለቤቶች የሚተላለፉ ፕሮጀክቶችን ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

52. ኤጀንሲው ወደ ሚመለከተው የተግባር ባለቤት ያስተላለፋቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊነታቸውን የሚከታተልበትና ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

53. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ ከግብአት ኩፖን ሽያጭ በስተቀር ሁሉም ፕሮጀክቶች ወደ ተግባር ባለቤቶች አልተላለፉም፡፡ ወደ ተግባር ባለቤቶች መተላለፉ የተገለፀው የአግሮሜት ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ ኤጀንሲው የሜትሮሎጂን

መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የአውቶማቲክ የአየር መመዝገቢያ ጣቢያ ተከላ በተመለከተ ያከናወናቸው ስራዎች በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስቱ ክልሎች (ትግራይ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ብ/ብ/ሕ) የአየር ትንበያ መረጃዎችን በመተንተን በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ የተጠቀሰው ፕሮጀክት ለተግባር ባለቤት ስለመተላለፉ የሚያመለክት ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

54. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው ኤጀንሲው ወደ ተግባር ባለቤቶች የተላለፉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የአግሮሜት ፕሮጀክት በተለያዩ ወረዳዎች የተተከሉት መሳሪያዎች ዓላማ በዙሪያቸው ለሚገኙ አርሶአደሮች ብቻ የተተነተነ የአየር ሁኔታ መረጃ ማቅረብ ሳይሆን የብሔራዊ ሜቲዮሮሎጂ ኤጀንሲ የላቀ ጥራት ያለው መረጃ በማሰባሰብ ከባቢ ተኮር የሆኑ የአየር ትንበያ መረጃዎችን ማመንጨት እንዲችል ታስቦ የተነደፈ ፕሮጀክት መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Factsheet/ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

55. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ሰነዱ ላይ የተገለፀው የፕሮጀክቱ ዓላማ በየክልሉ ለሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች አስፈላጊውን የትንበያና ትንተና ምክረ-ሃሳቦችን በመስጠት በአካባቢያቸው ያሉ አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርብቶ አደሮች ተጠቃሚ ማድረግ በመሆኑ እዲሁም የአየር ትንበያ መሳሪዎቹ ለብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ስለመተላላፋቸው ወይም ስለመገናኘታቸው ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

56. ኤጀንሲው ወደ ተግባር ባለቤቶች የሚተላለፉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት አለመኖሩ ስለፕሮጀክቱ ጠቃሚነት፣ ተደራሽነት፣ ጥራት፣ እና ውጤት እንዳይታወቅ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ የሚገጥማቸውን ችግር በአፋጣኝ ሊፈቱ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ሶስት የግምገማ ምእራፎችን ማለፋቸውን በተመለከተ፣**

57. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶች ሂደት በሶስት ምዕራፍ የመነሻ ጥናት (Baseline study) ፤ የአፈፃፀም ግምገማ (Performance evaluation) እና የተፅዕኖ ግምገማ (Impact evaluation) በሚል ክፍሎ ግምገማ ሊያደርግ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶች ሂደት በሶስት ምዕራፍ የመነሻ ጥናት (Baseline study)፣ የአፈፃፀም ግምገማ (Performance evaluation) እና የተፅዕኖ ግምገማ (Impact evaluation) በሚል ከፍሎ ግምገማ ማድረግ የሚጠበቅበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በሶስት ደረጃ ከፍሎ ግምገማ ስለማድረጉ ማስረጃው ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ማቅረብ አልቻለም፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች እና ህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሃላፊዎች (ዝርዝራቸው በአባሪ 3 ተያይዟል) ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን በሶስት ምእራፎች መሰረት ግምገማ በማድረግ እንዲያውቁት ያደረጋቸው ፕሮጀክቶች አለመኖራቸውን፣ በክልላቸው/በወረዳቸው ስለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የተደረገ ግምገማ አለመኖሩ እና ይህ ባለመሆኑም ፕሮጀክቱ ያመጣውን ተፅኖ ማወቅ እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው ገልፀዋል፡፡

60. ስለ ሁኔታው የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የፕሮጀክቶች የመነሻ ጥናት በተሟላ ሁኔታ አለመኖሩን ነገር ግን ማንኛውም ፕሮጀክት Situational analysis እንዳለው፣ የአፈፃፀም ግምገማ ስርዓቱ እንዳለና በየወሩ ለሲኒየር ማኔጅመንት ሪፖርት እንደሚቀርብ፣ የተፅዕኖ ግምገማ ግን ኤጀንሲው ካለው የቆይታ ጊዜ አንፃር ለመገምገም የማይቻል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

61. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ሊቀርብ ባለመቻሉ እና የተፅዕኖ ግምገማ እንደ ሴክተር ሳይሆን እንደ ፕሮጀክት ያደረገው ግምገማ የተጠየቀ በመሆኑና በተጠየቀው መሰረት የተዘጋጀ ማስረጃ ባለማቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

62. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ማንኛውም ፕሮጀክቶች በመመሪውያ ላይ በተቀመጠው ሶስት ምዕራፎች መሰረት ግምገማ አለማድረጉ ፕሮጀክቶች ያሉበትን ሂደት በጊዜ በማወቅ የማስተካከያ እርምጃ እንዳይወስድ እና በመቋረጥ ምክንያት አለአግባብ የሆኑ ወጪዎች እንዲከሰቱ ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው ፕሮጀክቶችን ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት አፈጻጸማቸው ላይ ግምገማ ማድረጉን በተመለከተ፣**

63. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶች ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ ውጤታማነትና ያስገኙትን ስኬት ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መስፈርት መሰረት መገምገም አለበት ፡፡

64. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ለታዩ የግብርና ግብአት መከታተያ፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የቀጥታ ዘር ግብይት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት፣ የግብርና አገልግሎት ማዕከል፣ ሞዴል የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል አቅም ግንባታ፣ የግብአት ኩፖን ሽያጭ እና አውቶሜት ኢ-ቫውቸር ሲስተም፣ የምጥን ማዳበሪያ እና የህብረት ስራ ማህበራት አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችን ግምገማ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

65. ከዚህ ጋር ተያይዞ ኤጀንሲው በራሱ በቀጥታ የሚያስፈጽማቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የእያንዳንዱን ፕሮጀክት ከአመታዊ ግቡ አንጻር የደረሱበትን ደረጃ በትክክል በሚያሳይ መልኩ ዝርዝር መግለጫ በማካተት ያሉበትን አፈጻጸም ለመመዘንና ድጋፍ ለማድረግ በሚያስችል መንገድ ሪፖርቱ ውስጥ አካትቶ ባለመዘጋጀቱ ማስተካከያ እንዲያደርግ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው በ2009 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ ዓመት በትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ግብረ-መልስ ላይ አስተያየት እንደተሰጠው ነገር ግን እንዳላስተካከለ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች እና ህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች በክልላቸው በሚገኙ ወረዳዎች ኤጀንሲው ተግባራዊ እያደረጋቸው የሚገኙ ፕሮጀክቶች ውጤታማነታቸውን ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት በየአመቱ ስለመገምገማቸው እንደማያውቁ እና የግምገማ ሪፖርቶች ደርሰዋቸው የማያውቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

67. ስለ ሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ትግበራ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በየዓመቱ እንደሚገመግም እንዲሁም የፕሮጀክቶችን ተግባራት በተለየ ሁኔታ እና ዘርዘር ባለ መልኩ አፈፃፀማቸውን በመገምገም ለቋሚ ኮሚቴው እንደሚያቀርብ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/ በሰጡት አስተያየት ገልፀዋል፡፡

68. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን እያንዳንዳቸውን ፕሮጀክቶች (በተለይ የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ጋር ተያይዞ ያሉትን) በየወሩ፣በየሩብ ዓመቱ እና በየዓመቱ ቀድመው በተቀመጡ አመላካቾች መሰረት ግምገማ ያደረገበትን ሪፖርት ማስረጃ ባለማቅረቡ፣ በራሱ የሚያስፈጽማቸው ፕሮጀክቶች ተግባራት በተለየ ሁኔታ እና ዘርዘር ባለ መልኩ ለቋሚ ኮሚቴው እንደሚያቀርብ ቢገልፅም እንደማስረጃነት ያቀረበው የቀጥታ ዘር ግብይት ሂደትን

ለማስፋፋትና ተቋማዊ ማድረግን በተመለከተ በ2008/09 በአማራ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ወረዳዎች ግምገማ መደረጉን ብቻ የሚያሳይ እንጂ የሌሎቹን ስለማያካትት፣ የተዘጋጀውም ሪፖርት ለቋሚ ኮሚቴው ስለመላኩ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

69. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚቀርፃቸው ፕሮጀክቶች በየጊዜው ግምገማ አለማድረጉ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ የሚያጋጥሙዋቸው ችግሮች ሲኖሩ በወቅቱ መፍትሄ እንዳያገኙ፣ የችግሮች መፍትሄ አለማግኘት ደግሞ አግባብ ላለሆነ የፕሮጀክት ወጪ፣ ለመቋረጥ እና ለተለያዩ ብክነቶች እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

## 2.2 ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት፣ ከአገር አቀፍና ከአለም አቀፍ የግብርና ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፣

### የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ

70. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ባለድርሻ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በሚተገብሩበት ወቅት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው፡-

- በስትራቴጂዎች ውስጥ የተቀመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች (የፖሊሲ ማሻሻያ፣ አሰራሮች) ባለድርሻ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በሚተገብሩበት ወቅት ተግባራዊ ማድረጋቸውን በስልጠና እና በመስክ ክትትል እና ድጋፍ እንደሚያደርግ ቢገልፅም ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣
- በሚያዘጋጃቸው እና በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ላይ በተመሳሳይ የስልጠና ዓይነቶች ተመሳሳይ ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ እንዲሳተፉ የሚያደርግ መሆኑ፣
- የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ (የገብስ፣የጤፍ፣ስንዴ፣በቆሎ ወ.ዘ.ተ) ስትራቴጂዎች ኤጀንሲው በአዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ያልላከ ሲሆን እነዚህን ስትራቴጂዎች ተጠቃሚዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ማለትም (በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ ወ.ዘ.ተ) እንዲተረጎሙ በማድረግ ተጠቃሚዎች

እንዲደርሳቸው ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ይህንን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው የታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች እና ህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ ማስረጃውን ባያቀርቡም ስልጠና እንደተሰጣቸው የገለፁ ሲሆን ስትራቴጂዎችን በተመለከተ ግን ምንም አይነት ሰነድ እንዳልደረሳቸው ገልፀዋል፡፡

73. ስለ ሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ተግባራዊ መደረጋቸውን በመስክ ክትትል እና በትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች እቅድ ዝግጅት ወቅት ተገቢውን ድጋፍ እንደሚያደርግ፣ በተለያየ ጊዜ የሚወጡ ዶክመንቶች ለተለያዩ አስፈፃሚ አካላት በተለያየ ጊዜ መላካቸውን፣ ስትራቴጂዎች ለአጠቃቀም ምቹ እንዲሆኑም በቀጣይ በፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ /አማርኛ/ ለመተርጎም ጥረት እንደሚደረግ፣በሌሎች የክልል ቋንቋዎች የመተርጎም ስራ ግን የክልል ባለድርሻ አካላት ሃላፊነት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

74. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚነደፉ ስልቶች ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ተግባራዊነት አፈፃፀማቸውን በመስክ ክትትል ስለማድረጉ፣ የሚወጡ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎችና ሌሎች ሰነዶች ለአስፈፃሚ አካላት መላኩን ይገልጻል ተብሎ የቀረበው የmaize value chain strategy ማስረጃ ስትራቴጂውን በተመለከተ በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስትሩ የተሰጠው አስተያየት እንጂ ለእያንዳንዱ አስፈፃሚ በትክክል መላኩን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

75. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የተቀረጹ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎች ወዘተ ፈፃሚ አካላት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል በማድረግ ያሉባቸውን ክፍተቶች ግብረ-መልስ በመስጠት አለማሳወቁ፣ ፖሊሲ እና እስትራቴጂዎቹ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በየጊዜው የሚነደፉ ስትራቴጂዎችን ፈፃሚዎች ሊረዱ በሚችሉበት ቋንቋ በማዘጋጀት እንዲደርሳቸው አለማድረጉ ፖሊሲው እና እስትራቴጂው ተደራሽ እና ተፈጻሚ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ በዘርፉ ለመድረስ የታቀደው አላማ ግብ እንዳይመታ ያደርገዋል፡፡

**ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ የሚያስችል ዕቅድ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፣**

76. ኤጀንሲው ትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ የሚያከናውናቸው ተግባራት በመለየት ለመፈፀም የሚያስችል ዝርዝር ተግባራትን የያዘ የራሱ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

77. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ ኤጀንሲውን የሚመለከቱ እና የሚያከናውናቸው ተግባራት የሚያሳይ የራሱ እስትራቴጂክ እቅድም ሆነ አመታዊ ዕቅድ እንዳላዘጋጀ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

78. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የኤጀንሲው ኃላፊነት የራሱን እቅድ ለማቀድ የማይመች በመሆኑ ምክንያት የራሱን እቅድ ማዘጋጀት አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

79. ኤጀንሲው ከአገር አቀፍ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የራሱን ድርሻ በመውሰድ የሚሰጠውን ድጋፍና በተመለከተ የሚያከናውናቸው ተግባራት የራሱን እቅድ በማዘጋጀት ድጋፍ አለመስጠቱ ለአጀንዳው የሚያደርገውን ድጋፍ ወይም ያለውን አስተዋፅኦ በግልፅ እንዳይታወቅ እንዲሁም በእቅድ መሰረት ያልተከናወኑ ተግባራት ሲኖሩ ተጠያቂ እንዳይሆን ያደርገዋል፡

**ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ለማስፈጸም የሚያከናውናቸው ተግባራትን መገምገሙን በሚችልበት መንገድ ማስቀመጡን በተመለከተ፣**

80. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ሊያስቀምጥና በመስፈርቱ መሰረት ሊገመግም ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ

- የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ስትራቴጂክና አመታዊ እቅድ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ተግባራት ሊለኩ በሚችሉበት ማለትም የእቅድ አፈፃፀም ላይ ያሉ ተግባራት ከእቅዱ ጋር ለማነፃፀር በሚያስችል መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- ቀደም ሲል ኤጀንሲው ፕሮጀክቶቹን ለግምገማ ሲጠቀምበት የነበረው (አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ) በሚል ብቻ ይገለፅ የነበረው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት አፈፃፀም መለኪያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ከ50 በመቶ

በታች ቀይ (እጅግ የዘገዩ)፣ ከ50-70 በመቶ ቢጫ (በመጠኑ የዘገዩ) እና ከ75 በመቶ በላይ አረንጓዴ (በጥሩ አፈፃፀም) ያሉ በሚል በማስተካከል በ2009 የአጀንዳው ዓመታዊ አፈፃፀም ላይ የተጠቀመበት ቢሆንም ይህ ገደብ (range) የተግባሩን አጠቃላይ ሁኔታ እንጂ እያንዳንዱ ተግባር ያለበትን ዝርዝር ሁኔታ ለመገምገም/ለማወቅ የማያስችል መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

82. ይህንን አስመልክቶ የኤጀንሲ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በቃለ መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የኤጀንሲው የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት በቁጥር ለማነፃፀር አስቸጋሪ በመሆኑ እና የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ የእቅዶቹ ባለቤቶች ዋናዎቹ የአጀንዳው ባለቤቶች እንደሆኑና የኤጀንሲው ሚና የሚለኩ ግቦች እንዲቀመጡ ድጋፍ መስጠት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

83. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የአጀንዳውን እቅድና አፈፃፀም በቁጥጥር ለማነፃፀር በሚያመች መልኩ ማዘጋጀት የተለመደ አሰራር በመሆኑና ለአጀንዳው ባለቤቶች ግባቸውን መሰረት በማድረግ እንዲሰሩ ድጋፍ ማድረጉን የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

84. የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት ሊለኩ በሚችሉበት መልኩ አለመቀመጣቸው ዘርፉ ከግብ ለማድረስ የተነሳበትን እና ሊደርስ ያሰበውን ደረጃ በግልፅ እንዳይታወቅ እና በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች በየትኛው ተግባር እንደሆነ በዝርዝር እንዳይታወቅ እና በወቅቱ በመገምገም መፍትሄ እንዳይሰጣቸው ያደርጋል፡፡

**ኤጀንሲው የተግባር ባለቤቶች የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ያጠና መሆኑን በተመለከተ፣**

85. ኤጀንሲው ለተግባር ባለቤቶች የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ሊያጠና እና በጥናቱ መሰረት ሊተገብር ይገባል፡፡

86. ኤጀንሲው ለአጀንዳ ባለቤቶች ክፍተታቸውን ለይቶ ድጋፍ ለማድረግ የሚያግዘው የድጋፍ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያላደረገ እና የተግባር ባለቤቶቹ በራሳቸው በአፈጻጸም ወቅት ችግሮች በሚገጥሟቸው ጊዜ በሚጠይቁት የድጋፍ ጥያቄ መሰረት ብቻ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

87. ስለሁኔታው የኤጀንሲው መሰረታዊ ተልዕኮ በሴክተሩ ውስጥ የሚታዩ መሰረታዊ ማነቆዎችን የመለየትና ለእነዚህም መፍትሔዎችን ማመላከት እንጂ የተግባር ባለቤቶችን ፍላጎት ማጥናት ግዴታ እንደሌለበት የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች

ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

88. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የሴክተሩ ችግር የሚመነጨው የተግባር ባለቤቶች ከሚያጋጥሙዋቸው የአፈፃፀም ችግሮች ስለሆነ ኤጀንሲው በዘርፉ የሚኖሩ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችሉ መፍትሄዎችን በማፈላለግ እንዲተግብሩ እና አፈጻጸመቸውንም መከታተል የሚጠበቅበት በመሆኑ፣ እነዚህ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ፈፃሚዎች ስራቸውን በተፈለገው ደረጃ መፈፀም እንዲችሉ ኤጀንሲው ፍላጎታቸውን በጥናት ለይቶ በማወቅ ድጋፍ ሊያደርግላቸው የሚገባ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

89. የኤጀንሲው የድጋፍ አሰጣጡ በጥናት ላይ የተመረኮዘ አለመሆኑ የድጋፍ አሰጣጡ ግልፅነት እንዳይኖረው፣ ለየትኛው የድጋፍ ዓይነት ይበልጥ ድጋፍ መሰጠት እንዳለበት፣ በአሰጣጡ ላይ ያለው ክፍተት ምን እንደሆነ እና በቀጣይ በየትኛው የድጋፍ ዓይነቶች ላይ ትኩረት ቢሰጥ ፈፃሚዎችን ሊያረካ እንደሚችል እንዳይታወቅ ያደርገዋል፡፡

**ለትራንስፎርሜሽን አጀንዳ የተግባር ባለቤቶች የተደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ፣**

90. ኤጀንሲው በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለዩ ተግባራትን ለሚፈፅሙ የተግባር ባለቤቶች (በስትራቴጂክ ዝግጅት፣ ዝርዝር ችግር በመፍታት፣ በአቅም ግንባታ፣ የማስተባበር፣ የቴክኒክ፣ የትንተና፣ የሥራ አፈፃፀም፣ የሀብት ማሰባሰብ/ ማስተዳደር እና የልዩ ሥራ) ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

91. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራትን የሚፈፅሙ የተግባር ባለቤቶችን ለመደገፍ Enhancing ATA's Transformation Agenda Deliverable (TAD) Implementation Support Model ቢያቀርብም በተዘጋጀው ሞዴል መሰረት ያደረገው ድጋፍ እንዲሁም ሞዴሉም በወረቀት ደረጃ ያለ እንጂ በተቀረፀው ሞዴል መሰረት የተሰሩ ስራዎችንም በተመለከተ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት አላቀረበም፡፡ በተጨማሪም በአስፈጻሚ አካላት የሚተገበሩና የትግባራ ክትትል የሚያደርግባቸው ተግባራት የስራው ባለቤት ለሆኑ ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን የማስፈፀም ድጋፍ መስጠት፣ በተቀመጠላቸው አቅጣጫ የሚተገብሩትን ስልት መደገፍና አፈጻጸማቸውን በመደገፍ የተግባሩ ባለቤቶች ጠንካራ ስራ ሰርተው ከጉድለቶቻቸው የሚወጡበትና ያልተፈፀሙ ተግባራት እንዲፈፀሙ ጠንካራ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት በቋሚ ኮሚቴው አስተያየት የተሰጠው ሲሆን በአስተያየቱ መሰረት ያደረገው ማስተካከያ

ስለመኖሩ ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ አላቀረበም፡፡

92. እንዲሁም ከሀብት ማስተዳደር ጋር ተያይዞ ኤጀንሲው

- በየክልሉ ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች የያዘውን የበጀት እና የጊዜ መጠን የማያሳውቅ መሆኑ፣
- በማዳበሪያ ፋብሪካዎች እና በሌሎችም ፕሮጀክቶች የሚገጥሙ የቴክኒክ ችግሮች ላይ ኤጀንሲው በወቅቱ ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ እና
- ኤጀንሲው በፕሮጀክቶቹ ሥራ ላይ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተግባር ባለቤቶች እንዲሳተፉበት እና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው ግንዛቤ ሊፈጥር አለመቻሉን

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የኦሮሚያ፣ ደቡብ እና ትግራይ ክልሎች የግብርና እና ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

93. ስለ ሁኔታው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በተቋሙ ያሉ ከማስፈጸም አቅም ጋር የተያያዙ ክፍተቶችን በተለይም የሰው ኃይሉ ላይ ያሉትን ክፍተቶች በመለየት የአቅም ግንባታ በማካሄድ የመደገፍ ሥራዎች ደካማ እና ያልተሰራ ሊባል በሚችል ደረጃ መሆኑን፣ በዚሁ አምድ ውስጥ የአካላዊ (እንደ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች) ድጋፍ ሚ/ር መ/ቤቱ እንዲያገኝ ከማድረግ አንጻር የተሰራው ሥራ ከሚጠበቀው ጋር ሲነጻጸር ደካማ መሆኑ፣ እንደ አብነት ለመግለጽ ሚ/ር መ/ቤቱ ከምርምር የሚመጡም ሆነ ሌሎች ምንጮች የሚገኙን ጠቃሚ የግብርና ቴክኖሎጂ በቀላል መንገድ እንዲደርስና እንዲላመድ ማድረግም ሆነ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላት ያላቸው አቅም ጎልብቶ እና የምርምር አንድ አካል ሆነው ለአርሶ አደሩ መፍትሄ ሰጪ ተቋም እንዲሆኑ ማስቻል ላይ የተሰራው ሥራ ደካማ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

94. ስለሁኔታው በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ (ዝርዝራቸው በአባሪ 3 ተያይዞል፡፡) አስፈፃሚ አካላት ማስረጃ ማቅረብ ባይችሉም ኤጀንሲ የስልጠና ድጋፍ ብቻ እንደሰጣቸው ነገር ግን በየጊዜው ለሚሰጣቸው ስልጠና ወጪዎች በግልፅ እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑን፤ መስጠት በሚገባው ሌሎች የድጋፍ አይነቶች ግን ምንም ድጋፍ አግኝተው የማያውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

95. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው

- የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራትን የሚፈጽሙ የተግባር ባለቤቶችን ለመደገፍ የተዘጋጀው ሞዴል በእቅድ ትግበራ ወቅት የትራንስፎርሜሽን

አጀንዳ ባለቤቶች እጅግ ሰፊና ሊተገበር የማይችል የድጋፍ ጥያቄ /የበጀት/ ለኤጀንሲው ከማቅረባቸው ጋር ተያይዞ ያጋጠመውን የኃላፊነት ወሰን በግልፅ ለማመላከት የተቀመጠ የአጭር ጊዜ መፍትሄ እንደነበር

- ይህን ሁኔታ እንደመነሻ በማድረግ በቀጣይ የተቀረጸውና በመተግበር ላይ ያለው የደሊቨሪ ዩኒት አሰራር የኤጀንሲውንና የአጀንዳ ባለቤቶችን ኃላፊነት በግልፅ በማስቀመጥ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት መቻሉን፣
- የፕሮጀክቶች በጀትም ሆነ የሰው ሃይል በእቅድ ዝግጅትና በትግበራ ወቅት ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ክልሎች/ወረዳዎች እንዲያውቁት እንደሚደረግ ነገር ግን አንዳንድ ፕሮጀክቶች በቀጥታ በኤጀንሲው ስለሚፈጸሙ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረግበት ክልል/ወረዳ እንዲያውቀው የሚደረግበት ሁኔታ አለመኖሩን
- ይህን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ በሰጠው አስተያየት መሰረት ከተለያዩ ፕሮጀክቶች አንፃር በመመልከት ትስስሮችን የበለጠ ለማጠናከር ጥረት እንደሚያደርግ

ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Factsheet/ `በሰጡት ምላሽ የገለፁ ሲሆን በቋሚ ኮሚቴው በተሰጠው አስተያየት መሰረት ያደረገውን ማስተካከያ በተመለከተ ምላሽ አልሰጠም፡፡

96. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የኤጀንሲውንና የአጀንዳ ባለቤቶችን ኃላፊነት በግልፅ በማስቀመጥ መሰረታዊ የሆነ ለውጥ ማምጣት ማስቻሉን የተገለፀው የደሊቨሪ ዩኒት፣ በቀጥታ ከሚያስፈፅማቸው ፕሮጀክቶች ውጪ ያሉትን ፕሮጀክቶች በእቅድ ዝግጅትና በትግበራ ወቅት ስለተያዘላቸው በጀት፣ የሰው ሃይል የመሳሰሉት ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ ለሚደረግባቸው ክልሎች/ወረዳዎች ያሳወቀበት ማስረጃ ሊያቀርብ ባለመቻሉ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

97. ኤጀንሲው ለድጋፍ ባለቤቶች በተለያዩ የድጋፍ ዓይነቶች ድጋፍ አለማድረጉ ፈፃሚዎች በዘርፉ ሊያስመዘግቡ የሚገባቸው ግቦች ላይ እንዳይደርሱ ራሱን የቻለ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ እንዲሁም የፕሮጀክቶቹን ጊዜ እና በጀት አለማሳወቅ ግልጸኝነት እንዳይኖር በማድረግ ገንዘቡ ለብክነት እንዲጋለጥ በር የሚከፍት ሲሆን ቴክኒካል ድጋፍ አለመደረጉ ፕሮጀክቶቹ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

**በሙከራ (Pilot) ደረጃ ተሞክረው የስራው ባለቤት እንዲያስፋፋቸው የተደረጉ ስራዎች መኖራቸውን በተመለከተ፣**

98. ኤጀንሲው በሙከራ /ፓይለት ደረጃ ሊሞከሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ከባለድርሻዎች

ጋር በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምግሞ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ሊያደርግና ሥራውን ሊደግፍ ይገባል፡፡

99. ኤጀንሲው ከጥምር እርሻ ሥርዓት (Clustering) በስተቀር በፓይለት ደረጃ ሊሞከሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምግሞ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ያደረጋቸው ስራዎች አለመኖራቸው በኦዲቱ ታውቋል፡፡

100. ስለሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የቀጥታ ዘር ግብይት በአማራ ክልል በፓይለት ደረጃ ተሞክሮ መስፋፋቱን፣ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ከሌላ ፕሮጀክቶች ጋር በማቀላቀል ለማስፋት እቅድ መያዙን ገልፀዋል፡፡

101. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የቀጥታ ዘር ግብይት መስፋፋቱንም ሆነ የግብር አገልግሎት ማዕከልን ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በማቀላቀል የማስፋት ስራን ለማከናወን የተያዘው እቅድ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

102. ኤጀንሲው በሙከራ ደረጃ ፕሮጀክቶችን ከፈፃሚ አካላት ጋር በጋራ በመሆን በማከናወን ውጤታማ መሆናቸው ሲረጋገጥ ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ በማድረግ በዘርፉ ያላቸው አስተዋፅኦ እንዳይጨምር እና በሙከራ ደረጃ ያሉት እንዳይስፈፉና የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

**በትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት ዙሪያ ፈፃሚ አካላት ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉን በተመለከተ፣**

103. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ አካላት ግንዛቤ እንዲያገኙ የተለያዩ መድረኮችን ሊያዘጋጅ እና የግንዛቤ መድረኮቹ ያስገኙትን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡

104. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ ላላቸው አካላት የሚያዘጋጃቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የወጣ ወጪ እና የተሳታፊዎችን ስታስቲካዊ መረጃ እንዲሁም ከተፈጠሩ መድረኮች በተግባራት አፈፃፀም ላይ የተገኘውን ውጤት የሚገመግምበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡

105. ይህን በተመለከተ ኃላፊዎቹ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የተሳታፊዎች መረጃ በየፕሮጀክቶቹ አመታዊ ሪፖርት ውስጥ ተካቶ እንደሚገኝ፣ ለመድረኮቹ የወጣው ወጪ የፋይናንስ አመታዊ ሪፖርት ላይ እንደሚገለጽ፣ የስልጠና ውጤታማነት ክትትል ስርዓቱ ግን የተሟላና ወጥ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

106. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የተሳታፊዎች ዝርዝር መረጃና የመድረኮች ወጪ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

107. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን አስመልክቶ የሚያዘጋጃቸው መድረኮች የተሳታፊዎች ዝርዝርና ለመድረኩ የወጣውን ወጪ አለማስቀመጡ አሰራሩ ግልፅነት እንደሌለው ከማሳየቱም በተጨማሪ በአጀንዳው ባለቤቶች ላይ ቅሬታን ይፈጥራል፡፡ የስልጠናው ውጤት ተለክቶ አለመታወቁ ለስልጠናው የወጣው ጊዜ እና ወጪ እንዲባክን በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

**ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣**

108. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትራንስፎሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን አስመልክቶ ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

109. ኤጀንሲው የትራንስፎሜሽን አጀንዳ እቅድና አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማጠናቀር ለትራንስፎሜሽን ካውንስሉ የሚልክ ቢሆንም፡-

- በትራንስፎሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ አስመልክቶ የሚያደርገው ክትትል ጠንካራ አለመሆኑ ለዚህም ማሳያ የአጀንዳው ባለቤቶች ያሉበትን ደረጃ በተመለከተ ፈፃሚዎች በየጊዜው ያሉበትን ደረጃ በጋራ እየገመገመ አፈፃፀማቸው ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ፣
- ለቋሚ ኮሚቴው የሚልከው የትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በአስፈጻሚ አካላት የሚተገበሩና የትግበራ ክትትል የሚያደርግባቸው ዘርፎች ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መፍትሄዎችን በሚያሳይ መልኩ ገምግሞ ሪፖርቱን ለቋሚ ኮሚቴው የማይልክ መሆኑንና መሻሻልም እንዳለበት ቋሚ ኮሚቴው አስተያየት የሰጠው ቢሆንም በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት ያደረገው ማስተካከያ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣
- የአጀንዳው ባለቤቶች ያሉበትን ደረጃ በመገምገም አስፈላጊውን ግብረ መልስ

የማይሰጥ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

110. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ አስፈፃሚ አካላት ከኤጀንሲው ጋር በጋራ አቅደው የማይሰሩ መሆኑን፣ በጋራ የሚከታተለው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እንደሌለ እና የክትትል ስርአትም እንዳልዘረጋ ገልፀዋል፡፡

111. ስለሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው በየሩብ ዓመቱ ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ በሪፖርት ለትራንስፎርሜሽን ካውንስሉ እንደሚያቀርብ፣ በእያንዳንዱ ስራዎች ላይ ባለሙያዎችን በመላክ ፈጻሚዎች ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በመለየት ቢጫ፣ አረንጓዴ እና ቀይ መሆኑን በመለየት ለትራንስፎርሜሽን ካውንስሉ እና ለፈፃሚ አካል የሚልኩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact sheet/ በሰጡት ምላሽ በሪፖርቶች ላይ የትግበራ ክትትል የሚያደርግባቸው ዘርፎች ላይ ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎችን ማካተትን በተመለከተ በቋሚ ኮሚቴው በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማስተካከያ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

112. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው ለትራንስፎርሜሽን ካውንስሉ አጠናቅሮ ከሚልከው ሪፖርት ውጪ በየሩብ ዓመቱ ባለሙያዎችን በመላክ ፈፃሚዎች ያሉበትን ደረጃ የሚያረጋግጥበት ማስረጃ ባለማቅረቡ፣የቋሚ ኮሚቴው በሰጠው አስተያየት መሰረት ሪፖርቶች ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን እንጂ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ያላካተተ በመሆኑ የተሠጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

113. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች ያሉበትን ደረጃ በየሩብ አመቱ የተጠናቀረ ሪፖርት ከመላኩ በፊት አፈፃፀማቸውን ከስር ከስር አለመከታተሉ በየሩብ ዓመቱ አቅደን ፈጽመናል ብለው የሚያቀርቡት ሪፖርት ታአማኒነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

**በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እና የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር መፈጠሩን በተመለከተ፣**

114. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር (በመረጃ፣ በልምድ ልውውጥ ወዘተ) እንዲፈጠር ማድረግ አለበት ፡፡

115. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር (በመረጃ፣ በልምድ ልውውጥ ወዘተ) እንዲፈጠር ያላደረገ፣ በየደረጃው ባሉ የግብርና ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ለማጠናከር ዘላቂነት ያለው መድረክ ያላዘጋጀ እና በተለያዩ ቦታዎች ከተለያዩ የመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በጋራ በመሆን የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ለክትትልና ለማስፋት በሚመች መልኩ የሚተገበሩ አለመሆናቸው በኦዲቱ ታውቋል፡፡

116. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ፈፃሚዎች የመስክ ጉብኝት ሲደረግ ኤጀንሲው በየክልሉ ተግባራትን ለማከናወን ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓት የሌለው ማለትም ፕሮጀክቱን በባለቤትነት የሚያስቀጥሉ አካላት ከፕሮጀክት ቀረጻ ፣ ትግበራ እና ግምገማ ድረስ ባሉ እንዲሳተፉ አለማድረጉ፣ በክልሉ የሚሰሩ የፕሮጀክቶች ብዛት፣ የተመደበላቸው የገንዘብ መጠን እና የሰው ሀይል እንዲሁም ከክልሎች ለፕሮጀክቶቹ መደረግ ያለበትን ድጋፍ በግልጽ እንዲያውቁት አለማድረጉ፣ከክልሎች እውቅና ውጭ ተግባራትን የሚያከናውን፣ ታች ካሉ ባለሙያዎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ክፍተት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የአሰራር ግልፀኝነት ችግር ያለበት፣በአስፈፃሚ አካላት መካከል ከመድረክ በዘለለ ጥብቅ ትስስር እንዲኖር የማያደርግ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

117. የትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈፃፀም በሚገመገምበት ጊዜ በ2008 በጀት ዓመት በኤጀንሲው አስተባባሪነት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብና ለማስተዋወቅ የጋራ መድረክ ማቋቋም የሚል ተግባር ስር በቁልፍ ባለድርሻ አካላት መካከል ዘላቂነት ያለው መድረክ ለማቋቋም የባለድርሻ ውይይት እንደሚደረግ ታቅዶ ያልተከናወነ፣ በ2009 ዓ.ም እቅድም ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

118. ኤጀንሲው የግብርና ትራንስፎርሜሽን ክላስተር ፕሮግራምን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይበልጥ ትኩረት በመስጠት እንዲሁም በምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካዎች ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሮቹ ተፈተው ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ እንዳለበት ቋሚ ኮሚቴው ለ2009 ዓ.ም አፈፃፀም በሰጠው ግብረ-መልስ ቢገልፅም በዚህ ዙሪያ ማስተካከያ ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ከታዩ ምጥን ማዳበሪያዎች ፋብሪካዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

119. ኤጀንሲው ትራንስፎርሜሽን አጀንዳን በማስፈፀም እና የመፍትሄ ሀሳቦችን አቀናጅቶ

መተግበር ላይ ያተኮረ በየሴክተሮቹ ጠንካራ ትስስር በመፍጠርና የመፍትሄ ሀሳቦችን አቀናጅቶ መተግበር ድክመት ያለበት እንደሆነና እዚህ ላይ በማተኮር ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ መሰራት እንደሚጠበቅበት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው ለ2009 ዓ.ም አፈፃፀም በሰጠው ግብረ-መልስ የተገለፀ ቢሆንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ያላሻሻለ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

120. ይህን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው የታዩ አስፈፃሚ አካላት በራሳቸው ጥረት ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ሊረዱዋቸው የሚችሉ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት መካከል ትስስር ለመፍጠር የራሳቸውን ጥረት እንዳደረጉ ነገር ግን በኤጀንሲው አማካይነት ምንም ዓይነት ትስስር እንዳልተፈጠረላቸው ገልፀዋል፡፡

121. ስለሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ Agriculture commercialization cluster ላይ value chain alliance የሚል መድረክ እንዳለና በዚህ መድረክ ላይ የግብርናው ዋና ተዋናዮች እንዲገኙ እንደሚያደርግ በተጨማሪም ዝርዝር መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ የሚያደርስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

122. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መድረኩ የተፈጠረ ስለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

123. ኤጀንሲው በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር አለማድረጉ በተፈጠረላቸው ትስስር ጠንካራ ስራ እንዳይሰሩ የሚያደርግ ሲሆን ይህም በዘርፉ ላይ ሊመጣ የታሰበው ለውጥ እንዳይመጣ የራሱን የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

## ክፍል ሦስት

### *መደምደሚያ*

124. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለትራንስፎሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ለመስጠት የሚነድፋቸው ስልቶች ሊተገበሩ የሚችሉ እና የሚነድፋቸው ስልቶች ዕድገትን፣አካባቢያዊ ዘላቂነት፣ አስተማማኝ የገበያና የምርት ማቀነባበር ብቃት እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ አለመሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚያደርጋቸው ጥናቶች የአነስተኛ አርሶ አደሩን እና የፈፃሚዎችን ፋላጎት እና አቅም መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣ ለዚህም ማሳያ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ፕሮጀክት እ.አ.አ ሚያዝያ 2016 ተጀምሮ መጋቢት 2018 መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም ፕሮጀክቱን ለመጀመር ስትራቴጂ ተቀርጸ ነገር ግን የአርሶ አደሩን አቅም ያላገናዘበ እና አርሶ አደሩ አቅሙን ለማጎልበት የሚያስችል ሌሎች አማራጮች ባለመኖራቸው ወደ ተግባር ያልተገባ መሆኑ፣ በተጨማሪም ያከናወናቸው ጥናቶች በሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ከቀጥታ ዘር ግብይት በስተቀር ሌሎች ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ቦታዎች (ክልል፣ ዞን እና ወረዳ) የሚመርጥበት መስፈርት የሌለው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን የትግበራ ቅድመ-ዝግጅት (Implementation set-up) ሙከራና ማሻሻያ (testing and refinement) እና ማስረከብ (handover) የሚሉ ሶስት የትግበራ ደረጃዎች እንዲያልፉ ስለማድረጉ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የረጅም ጊዜ ተግባር ባለቤት (deliverable owner) ያስተላለፈው ፕሮጀክት የሌለ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ወደ ሚመለከተው የተግባር ባለቤት የሚተላለፉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚከታተልበትና ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን በሶስት ምዕራፍ የመነሻ ጥናት (Baseline study) ፣ የአፈፃፀም ግምገማ (Performance evaluation) እና የተፅዕኖ ግምገማ (Impact evaluation) በሚል ከፍሎ ግምገማ ስለማድረጉ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በየአመቱ እና በአመት ሁለት ጊዜ የፕሮጀክቶችን ውጤታማነትና ያስገኙትን ስኬት ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት የማይገመግም መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በየአመቱ እና በአመት ሁለት ጊዜ ውጤታማነታቸውን እና ያስገኙትን ስኬት ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት የማይገመግም መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በስትራቴጂዎች ውስጥ የተቀመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች (የፖሊሲ ማሻሻያ፣ አሰራሮች) ባለድርሻ አካላት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በሚተገብሩበት ወቅት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣
- የሰብል ምርትና ምርታማነት ይረዳሉ ብሎ ያዘጋጃቸው (የገብስ፣የጤፍ፣ስንዴ፣በቆሎ ወ.ዘ.ተ) ስትራቴጂዎች በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች አለመላኩን እና እነዚህን ስትራቴጂዎች በአገራችን ቋንቋዎች (በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ ወ.ዘ.ተ) ተተርጎሞ ለተጠቃሚው ምቹ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጁ ያላደረገ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ የሚያከናውናቸው ተግባራት በመለየት ለመፈፀም የሚያስችል ዝርዝር ተግባራትን የያዘ የራሱ እቅድ የሌለው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የተግባር ባለቤቶች የሚያስፈልጋቸውን የድጋፍ ዓይነት ለማወቅ የሚያስችለው የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ያላጠና መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለዩ ተግባራትን ለሚፈፅሙ የተግባር ባለቤቶችን ለመደገፍ Enhancing ATA's Transformation Agenda Deliverable (TAD) Implementation Support Model ቢያቀርብም በተዘጋጀው ሞዴል መሰረት ያደረገው ድጋፍ እንዲሁም ሞዴሉም በወረቀት ደረጃ ያለ እንጂ በተቀረፀው ሞዴል መሰረት የተሰሩ ስራዎችንም

በተመለከተ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣

- ኤጀንሲው ከክላስተሪንግ በስተቀር በፓይለት ደረጃ ተሞክሮ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ያደረገው ስራ አለመኖሩ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ ላላቸው አካላት የሚያዘጋጃቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የወጣ ወጪ እና የተሳታፊዎችን ስታስቲካዊ መረጃ እንዲሁም ከተፈጠሩ መድረኮች በተግባራት አፈፃፀም ላይ የተገኘውን ውጤት የሚገመግምበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ አስመልክቶ ሪፖርታቸውን በማጠናቀር ለትራንስፎርሜሽን ካውንሱሉ ከመላክ ውጪ ፈፃሚዎች በየጊዜው ያሉበትን ደረጃ በጋራ እየገመገመ አፈፃፀማቸው ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር (በመረጃ፣ በልምድ ልውውጥ ወዘተ) እንዲፈጠር ያላደረገ መሆኑ፣

125. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

126. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችና ለትራንስፎሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ➢ ኤጀንሲው ለሰብል ምርትና ምርታማነት እድገት ማነቆ የሚሆኑ ችግሮች በተደጋጋሚ ሊከሰቱ የሚችሉ በመሆናቸው ችግሮች በየጊዜው በጥናት ሊለይ ይገባል፡፡ ችግሮችን ለመፍታት የሚነድፋቸው ስልቶች አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ሊያደርግና አገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ያላትን አስተዋፅኦ እንዲጨምር ሊያደርግ በሚችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡
- ➢ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚያከናውናቸው ጥናቶች የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ፍላጎትና አቅም እንዲሁም በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ በየጊዜው የሚያከናውናቸው ጥናቶችም ተግባራዊ መደረጋቸው የአሰራር ስርአት ዘርግቶ መከታተል ይኖርበታል፡፡
- ➢ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ በአራቱም ክልሎች በሚገኙ ወረዳዎች ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ፕሮጀክቶች ለያንዳንዳቸው ፕሮጀክቶች እንደ አይነታቸው ወረዳዎችን የሚመርጥበት መስፈርት በማዘጋጀት በመስፈርቱ መሰረት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ሊያደርግ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው ክልሎች/ወረዳዎች ደግሞ ስለተመደበላቸው በጀት በግልፅ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡
- ➢ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን በሶስቱ የትግበራ ደረጃዎች ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- ➢ ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶችን ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት በማጠናቀቅ እና የረጅም ጊዜ ባለቤቶች በራሳቸው ሊፈፅሙ እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ድጋፍ በማድረግ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሚደረጉባቸው ወረዳዎች የሚገኙ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ➢ ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለማሳካት የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጠቃሚ እንደሆኑ አምኖ የመረጣቸውን ፕሮጀክቶች ሙከራ


በተቀመጠላቸው የጊዜ በማጠናቀቅ የረጅም ጊዜ ባለቤቶች እንዲያስፋፉ ሊያስተላልፍና የተግባር ባለቤቶቹ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

- ኤጀንሲው የሚያከናውነው ማንኛውም ፕሮጀክት በመመሪያ ላይ በተቀመጡ ሶስት ሂደቶች መሰረት ግምገማ በማድረግ የፕሮጀክቱን ቀጣይነት በጊዜ በማወቅ ለፕሮጀክት ተብለው የሚወጡ አለአግባብ ወጪዎችን መቀነስ ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት በአመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ በመገምገም ፕሮጀክቶች ያሉባቸውን ግድፈቶች በወቅቱ እንዲያስተካክሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን ስልት መንደፍና የሚነደፉ ስልቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን መከታተል ያለበት እንደመሆኑ አገሪቱ ግብርናውን ለማዘመን የነደፈቻቸውን ስልቶች በፈፃሚ አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን ወይም አለመደረጋቸውን በየጊዜው በመከታተል በአፈፃፀም ወቅት የሚገጥማቸውን ችግሮች ሊፈታ ወይም እንዲፈቱ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት ለመደገፍ የሚያስችለውን ዝርዝር ተግባራትን የያዘ እቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ወደ ተግባር በመግባት አፈጻጸሙን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ሊያስቀምጥ ወይም የአጀንዳው ባለቤቶች እንዲያስቀምጡ ድጋፍ በማድረግ እቅድና አፈፃፀሞችን በማነፃፀር የተገኙ ድክመቶች በወቅቱ እርምት እንዲሰጥባቸው ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው ለትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ባለቤቶች የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ ፍላጎታቸውን በየጊዜው በማጥናት ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ተግባራት የሚፈፅሙ አካላት ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ በተለያዩ የድጋፍ አይነቶች (በስትራቴጂክ ዝግጅት፣ ዝርዝር ችግር በመፍታት፣ በአቅም ግንባታ ፣ የማስተባበር፣ የቴክኒክ፣ የትንተና ፣የሥራ አፈፃፀም፣ የሀብት ማሰባሰብ/ማስተዳደር እና የልዩ ሥራ) ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ ሥራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምግሞ ቀጣይነቱ ሲረጋገጥ ብቻ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ ላላቸው አካላት የሚያዘጋጃቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የወጣ ወጪ እና የተሳታፊዎችን ስታስቲካዊ መረጃ እንዲሁም ከተፈጠሩ መድረኮች በተግባራት አፈፃፀም ላይ የተገኘውን ውጤት የሚገመግምበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ኤጀንሲው ግብርናውን ለማሳደግ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን የሚፈፅሙ አካላትን የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት ስርዓት በመዘርጋት በአፈፃጸማቸው ወቅት ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች እንዲፈቱ ሊያደርግ ወይም የሚፈቱበትን መንገዶች ማመላከት ይኖርበታል፡፡
- ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ውጤታማ ለማድረግ ከሚሰሩም ሆነ ግብርናውን ለማዘመን በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ በግብርና ላይ የሁሉም አካላት ተሳትፎን በማጠናከር በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው አገሪቱ ልትደርስ ያቀደችው ግብ እንዲመታ የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት፡፡

በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፣ በኦዲት ወቅት ለታዩት ለኦሮሚያ፣ ትግራይና ደቡብ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮዎች እና ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች፣ በናሙና ተመርጠው ለታዩ ፕሮጀክቶች ባለሙያዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1፡ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 2፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች /Eva/Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥናትና በምርምር ለመለየት እንዲሁም ፕሮጀክቶችን ለመቅረጽ እና ተግባራዊነታቸውን ለመከታተል የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤ 1.1 ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች መከናወናቸውን እና የሚፈቱበትን ስልት በመቀየስ እንዲተገበሩ ማደረጉን መገምገም፣ | 1. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በጥናት ሊለይ ይገባል፡፡ |
| | 2. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ ችግሮችን በጥናት ከለየ በኋላ የሚፈቱበት ስልት እንዲነደፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ኤጀንሲው የሰብል ምርት እና ምርታማነት ለማሳደግ የሚነድፋቸው ስልቶች ዕድገትን ፣ አካባቢያዊ ዘላቂነት፣ አስተማማኝ የገበያና የምርት ማቀነባበር ብቃት እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚያካትት መሆኑን ባረጋገጠ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 4. በኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች የአነስተኛ አርሶ አደሩን እና የፈፃሚዎችን ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እና ሊተገበሩ የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 5. ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያከናወናቸው ጥናቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| 1.2 ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ፕሮጀክቶችን የሚቀርጽበት፣ የሚተገብርበትና ክትትል የሚያደርግበት እንዲሁም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋና | 6. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ በኃላፊነት የሚመራቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ቦታ (ክልል፣ ዞን እና ወረዳ) የሚመርጥበት ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 7. ኤጀንሲው የሚመራቸው ማንኛውም ፕሮጀክቶች በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን የትግበራ ቅድመ-ዝግጅት (Implementation set-up) ሙከራና ማሻሻያ (testing and refinement) እና ማስረከብ (handover) በሚል የተቀመጡ ሶስት የትግበራ ደረጃዎችን |

| | |
|---|---|
| ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣ | ማለፍ እንዲያልፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ለሚመለከተው የረጅም ጊዜ ተግባር ባለቤት (deliverable owner) የስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡ |
| | 9. ኤጀንሲው ወደ ሚመለከተው የተግባር ባለቤት ያስተላለፋቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊነታቸውን የሚከታተልበትና ድጋፍ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 10. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶች ሂደት በሶስት ምዕራፍ የመነሻ ጥናት (Baseline study) ፣ የአፈፃፀም ግምገማ (Performance evaluation) እና የተፅዕኖ ግምገማ (Impact evaluation) በሚል ክፍሎ ግምገማ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 11. ኤጀንሲው በየአመቱ እና በአመት ሁለት ጊዜ የፕሮጀክቶችን ውጤታማነትና ያስገኙትን ስኬት ቀድመው በተቀመጡ የውጤት አመላካቾች መሰረት መገምገም አለበት ፡፡ |
| 2. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ እና ፕሮጀክቶችን ለሚተገብሩ አስፈፃሚ አካላት (Deliverable owners) የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን ማጣራት፣<br>2.1 ኤጀንሲው በሰብል ምርትና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ የትራንስፎሜሽን አጀንዳዎችን ለሚተገብሩ አስፈፃሚ አካላት (Deliverable owners) ድጋፍ የሚያደርግ እና አፈፃፀማቸውን | 12. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያ /ጋይድላይኖች/ ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 13. ኤጀንሲው ትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለመደገፍ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በመለየት ለመፈፀም የሚያስችል ዝርዝር ተግባራትን የያዘ የራሱ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 14. ኤጀንሲው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ እቅድ እና አፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን ሊለኩ በሚችልበት መንገድ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ |
| | 15. ኤጀንሲው ለተግባር ባለቤቶች የድጋፍ ፍላጎት ደሰሳ ጥናት ሊያጠና እና በጥናቱ መሰረት ሊተገብር ይገባል፡፡ |
| | 16. ኤጀንሲው በግብርና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለዩ ተግባራትን ለሚፈፅሙ የተግባር ባለቤቶች (በስትራቴጂክ ዝግጅት፣ ዝርዝር ችግር በመፍታት፣ በአቅም ግንባታ ፣ የማስተባበር፣የቴክኒክ ፣የትንተና፣የሥራአፈፃፀም፣የህብትማሰባሰብ/ማስተዳደርእና የልዩሥራ) ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 17. ኤጀንሲው በፓይለት ደረጃ ሊሞከሩ የሚገባቸውን ሥራዎች ከባለድርሻዎች ጋር በጋራ በመሆን ካከናወነ በኋላ ውጤቱ ተገምግሞ የስራው ባለቤት እንዲያሰፋው ሊያደርግና |

| | |
|---|---|
| የሚከታተል መሆኑን መገምገም፣ | ሊደግፍ ይገባል፡፡ |
| 2.2ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት (የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ፣የክልል ግብርና ቢሮዎች፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የህብረት ስራ ኤጀንሲዎች ወዘተ)፣ከአገር አቀፍና ከአለም አቀፍ የግብርና ተቋማት ጋር የሰብል ምርትና ምርታማነትን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሠራበት አሠራር ሥርዐት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ | 18. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግን አስመልክቶ በትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ላይ በተቀመጡ ተግባራት ዙሪያ ፈጻሚ አካላት ግንዛቤ እንዲያገኙ የተለያዩ መድረኮችን ሊያዘጋጅ እና የግንዛቤ መድረኮቹ ያስገኙትን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡<br>19. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትራንስፎሜሽን አጀንዳው የተለዩ ተግባራትን አስመልክቶ ፈፃሚዎች የደረሱበትን ደረጃ የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡<br>20. ኤጀንሲው የሰብል ምርትና ምርታማነት አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ በግብርና ተዛማጅ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ልማቱን ለመደገፍ በሚቀረፁ ፕሮጀክቶች መካከል ጠንካራ ትስስር (በመረጃ፣ በልምድ ልውውጥ ወዘተ) እንዲፈጠር ማድረግ አለበት ፡፡ |

### አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላትና ፕሮጀክቶች ዝርዝር

| የክልሉ ስም | በክልሉ የታዩ ቢሮዎች | በክልሉ የታየው የፕሮጀክት ዓይነት |
|---|---|---|
| 1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት | ➢ የትግራይ ክልል ግብርና ቢሮ<br>➢ የትግራይ ክልል ህ/ስ/ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ<br>➢ እንዳሞሆኒ ወረዳ እርሻ ጽ/ቤት<br>➢ እንደርታ ወረዳ እርሻ ጽ/ቤት | ➢ አንድ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ ህ/ስ/ዩኒየን<br>➢ አንድ የማህበረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት<br>➢ አንድ የቀጥታ ዘር ግብይት |
| 2. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት | ➢ የኦሮሚያ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ<br>➢ የኦሮሚያ ክልል ህ/ስ/ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ<br>➢ የኦሮሚያ ክልል የግ.ት.ኤ ፎካል ፐርሰን/ጽ/ቤት<br>➢ የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን የግብርና መምሪያ<br>➢ የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን የህ/ስ/ማስፋፊያ ኤጀንሲ<br>➢ የወሊሶ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት<br>➢ የቶሌ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤት | ➢ አንድ ሞዴል ግብርና ማሰልጠኛ ማእከላት የአቅም ግንባታ<br>➢ አንድ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ<br>➢ አንድ የግብርና አገልግሎት ማዕከል |
| 3. በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት | ➢ የደቡ/ብ/ብ/ሕ ክልላዊ መንግስት እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ<br>➢ የደቡ/ብ/ብ/ሕ ክልላዊ ህ/ስ/ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ<br>➢ የሃዋሳ ዙሪያ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤት<br>➢ የሀዲያ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሃብት መምሪያ<br>➢ የሀዲያ ዞን ህ/ስ/ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ<br>➢ የስልጤ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሃብት መምሪያ<br>➢ የስልጢ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት<br>➢ የዶዮገና ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት<br>➢ የወራቤ ግብርና ምርምር ማዕከል | ➢ አንድ የግብአት መከታተያ ፕሮጀክት<br>➢ ሁለት የግብርና አገልግሎት መስጫ ማእከል<br>➢ አንድ የቀጥታ ዘር ግብይት<br>➢ አንድ የማህብረሰብ አቀፍ ዘር ማምረት<br>➢ አንድ የምጥን ማዳበሪያ ፋብሪካ (መልሀቅ)<br>➢ አንድ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት |